# ሰለ እግዚአብሔር ቃል መነቀፍ

አመሰግናለሁ፡ ወንድም ነቪሌ።

ወንድም ኔቪልን፡ “ዛሬ ጠዋት ትንሽ ቅባት አላገኘህም” አልኩት?

2 ለታመሙ ሰዎች ለመጸለይ ወደዚህ መጣሁ። እሁድ ጠ... ጠዋት ጥቂት ሰዎች ተሰብስበው ነበር። የታመሙ ሰዎችን፡ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ አደረኳቸው። ሁ—ሁል ጊዜ ለታመሙት በቤተክርስቲያን ውስጥ መጸለይ የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ። አላውቅም። ቤተክርስቲያን እወዳለሁ፡ ጉባኤ ወዳለበት፡ ሰዎች ወደ ሚጸልዩበት ቦታ መምጣት እወዳለው።

3 እዚያም አንድ ትንሽ ልጅ ነበረች፡ በጣም ቈንጆ ትንሽ ልጅ፡ አሁን፡ ሰዎች ወደ ቤታቸው ካልሄዱ፡ እዚህ የሆነ ቦታ ተቀምጣለች። ኦህ፡ አሁን አየኋት። በጣም ቈንጆ ምስኪን ነገር ነች። በጣም ታማ ነበር። የልሳን መልእክትና ትርጓሜው ሲነገር በመሰማት ላይ ሳለን፡ እየሰማን ነበር። እኛም እየሰማን ነበርና፡ ሰለ ትንሿ ልጅ የተነገረ ነገር እንዳለ ተረዳን። ምን ማለት እንዳለብን፡ ጌታ መልእክት ሰጥቶን እንደሆነ ለማየት እየጠበቅን ነበር። ነገር ግን ትንሿ ልጅ አሁን ደኅና እንደሆነችና፡ ደህና እንደምትሆን አምናለሁ። እ...

4 ሌላ ደግሞ፡ ዓይነ ሰውር የሆነች አንዲት ሴት ነበረች፡ ለእሷም እየጸለይንላት ነበርን። እዚያ አምቡላንስ ውስጥ ላለው ሰውዬም እንዲሁ፡ አገልጋይ ነው። ሰውየው ሰላሳ-አምስት ፓውንድ፡ ወይም አርባ ፓውንድ የሚመዝን አይመስለኝም። ሰ—ሰለዚህም፡ ለ... ለእነርሱ ለመጸለይ መጣሁ።

5 እና በተደጋጋሚ፡ ያቅማማሁበት ምክንያት፡ ከጥርሴ ውስጥ በጎደለው የተሞላው ሙሌት ሰለ ወደቀ ነው። ዛሬ ጥዋት፡ ከዚህ ከፊት ለፊት፡ ከጥርሴ በጎደለው ቦታ፡ የፋጨት ድምጽ ሳወጣ ነበር። ማስተከል እንዳለብኝና፡ በላያቸው ላይ ካፕስ ማድረግ እንዳለብኝ ነገሩኝ። ሰለዚህም እርጅና እየገሰገሰ መምጣቱ፡ የማውቀው ብቸኛው ነገር ነው። እዚህ ጋር ግማሽ የሚያኽል ቦታ፡ ሙሌት ነበረኝ፡ ማውራት ሰጀምር፡ ሊሰማችሁ ይችላል፡ ትንፋሽ በዚያ ባዶ ቦታ እየገፋ ይወጣል፡ ምን ለ—ለማለት እንደፈለኩ ታውቃላችሁ፡ በከንፈር በኩል እየገፋ ይወጣል። ያ ደግሞ እንደ ኮልታፋ፡ ያደርገኛል።

6 ዛሬ ጠዋት በሕይወት በመኖራችንና ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመምጣት በመቻላችን፡ ልዩ እድል የተሰጠን ህዝቦች ነን። በዚህ በገና ዋዜማ፡ የሚያከብሩትን በአል እየተጠባበቅን ነው፡ ይህም፡ ተ—ተሰፋ አደርጋለሁ... ዛሬ ጠዋት እዚህ ብዙ ልጆች አሉ፡ ሰለዚህ ዝም ብዬ እቆያለሁ። አያችሁ? እኛ አዋቂዎች፡ አንዳንድ ጊዜ፡ ልጆች መሰማት እንኳን የማይገባቸውን ነገሮች እንናገራለን፡ ታውቃላችሁ።

7 ነገር ግን፡ ከአፍታ በኋላ ቤተክርስቲያኒቱ ለህጻናት ትንሽ ሰጦታ፡ ያዘጋጀች ይመስለኛል። እዚያ ከኋላ፡ እያየሁት ነው። ኦህ፡ መቆየት ትፈልጋላችሁ። እሰከ ሰንበት ትምህርት በኋላ፡ ጠብቁ፡ እሺ፡ ምክንያቱም ዛሬ ጥዋት ለመሰጠት፡ ለህጻናት አንዳንድ ሰጦታዎች ያዘጋጁ ይ—ይመስለኛል። እኔም ይህን... እናንተ ህጻናት፡ እስታውሱ፡ ይህን ሰናደርግ፡ ይህንን ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ፡

ይህ ሳንታ ክላውስ አይደለም፡ ያ ተራ ታርክ እንደሆነ አንድ ቀን ትማራላችሁ ምክንያቱም ከሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ይሁን እንጂ ይህ ማለትም ከሁሉ በላይ እውነት ከሆነው፡ ከእግዚአብሔር ልጅ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ እያችሁ። ስለዚህ ዛሬ ጠዋት፡ ይህንን ትንሽ ሰጦታ እንሰጣችኋለን፡ ምክንያቱም አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሊሰጥ የሚችለውን ታላቅ ሰጦታ እንደሰጠ ያስታውቃችኋል፥ እርሱም ልጁን ነው። እኛ ይህን የምንገልጽበት መንገድ፡ እጅግ ደካማ ነው። ከዚህ ጋር ለማወዳደር የምንሰጠው ምንም ነገር የለንም። ነገር ግን ልክ እንደ ሟቾች፡ እርስ በርሳችን፡ ይህን እናደርጋለን።

8 አሁን፡ እስከሚቀጥለው እሁድ ድረስ ልጠብቅ ነበር። ምናልባትም፡ ለማለት የፈለግኩትን አንድ ነገር ለመናገር፡ እጠብቃለሁ። እና በቤት ውስጥ፡ በራእይ በኩል፡ መጠባበቅ ያለብኝ ነገር እንዳለ፡ አንዳች ነገር—ተገልጦልናል። ይህም የ... የሆነ፡ ከባድ ነገር፡ ይመስላል፡ ነገር ግን በጭራሽ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ከባድ ነው ብለን ማሰብ አንፈልግም። ቀ—ቀንበሩ ቀላል ነው።

9 ጌታ በዚህ አገልግሎት እንድንደሰት ከፈቀደልን፡ በ—በመጪው እሁድ፡ እግዚአብሄር ቢፈቅድ፡ እዚህ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ከመምጣቱ በፊት ፕሮግራም እናደርጋለን። የጠዋት አገልግሎት፡ ለታመሙ መጸለይ፡ ምናልባትም የጥምቀት አገልግሎት እንዲኖረን እንፈልጋለን። ከዚያም፡ ለጓደኞቻችን ማስታወቂያ አውጥተን፡ እነሱም እንዲመጡ ለማድረግ አሰብኩ። ከዚያም እሁድ ጠዋትና እሁድ ምሽት አገልግሎት ይኖረናል። ከዚያም ሰዎች ለአዲስ ዓመት ለመቆየት ይፈልጋሉ፡ ከዚያም... በዚህ ጊዜ፡ የምሽት ፕሮግራም ይኖረናል? [ወንድም ነቪል፡ "አዎን" አለ።—አርታዒ።]

10 እዚህ በአዲስ ዓመት ምሽት፡ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ፡ ንግግር ያሚያደርጉ በርካታ አገልጋዮች ይገኛሉ። እ—እንደዚህ ያሉ አገልጋዮች እንዲመጡ እና እንዲናገሩ እንጋብዛለን። እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ በአዲስ ዓመት ምሽት የሚነገር ነገር ካላቸው ሰዎች መካከል አንዱ መሆን እፈልጋለሁ።

11 ከዚያ በሚቀጥለው እሁድ፡ እየተደረጉ ያሉ ነገሮችንና፡ የተደረጉትን ነገሮችን፡ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ፡ እዚህ ቤተክርስቲያን እ—እምጥቼ እስከ ጫፍ ለማሳየት አስባለሁ።

12 ብዙዎቻችሁ በዚህ የገቢ ቀረጥ ጉዳይ ላይ እንዴት እያለፍን እንዳለ ተጨንቃችኋል። ተስተካክሏል። ያም እንዴት እንደተስተካከለ፡ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። እንደማስበው፡ በሚቀጥለው እሁድ፡ እንደገና መናገር ስለሚኖርብኝ፡ ስለዚህ እስከሚቀጥለው፡ እሁድ ድረስ እጠብቃለሁ። ዛሬ ጠዋት፡ ከቃሉ ክፍል፡ ትንሽ ልነግራችሁ እሞክራለሁ። እያችሁ? በመጪው እሁድ፡ እግዚአብሄር ቢፈቅድ፡ ይህ ሁሉ እንዴት እንደመጣ ለ—ለመንገር፡ እሞክራለሁ፡ ጌታ የተናገረውን እያንዳንዱን ነገር አመጣላችኋለሁ፡ በትክክል ኢላማውን ሲመታ፡ በትክክል በትክክለኛው ቦታ ሲቀመጥ አሳያችኋለሁ። እያችሁ? እርሱ አንዳች ክፉ ነገር አይናገርም።

13 ነገር ግን፡ አሁን፡ ዛሬ ጠዋት ልነግራችሁ የምፈልገው ነገር ቢኖር፡ ምናልባትም፡ እሁድ ልነግራችሁ የማልፈልገው ነገር፡ ትናንትና የሆነውን ነገር በተመለከተ ነው። ዛሬ ጠዋት ወደዚህ ስመጣ ልምጣ አልምጣ እያልኩ ነበር፡

ምክንያቱም ልቤ ተሰብሮ ነበር፡ ሰ—ስለዚህም ብዙም አልተሰማኝም። አሁን ግን መምጣቴ አልቀረ፡ እንግዲህ፡ የምችለውን ሁሉ እሞክራለሁ።

14 ከትናንት ወዲያ ምሽት፡ እንግዳ መጥቶብኝ ነበር፡ ወንድምና እኅት ሶትማን፡ እንደምናውቀው፡ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ባላደራዎች አንዱ ነው፡ ባለቤቱ እኔንና ባለቤቴን፡ ለመጠየቅ መጥታ ነበር። የጌታ ፈቃድ ቢሆን፡ በፊኒክስና በአካባቢው ስለሚደርገው ስብሰባዎች እያወራን ነበር። በግምት፡ እስከ አሥር-ተኩል ድረስ እያወራን ቆየን፡ ከዚያም አሰራ አንድ ስአት አከባቢ ተኛሁ።

15 ሌሊት፡ በሆነ ስአት አንድ ሕልም አየሁ። በዚህ ሕልም ውስጥ አባቴ ሊሆን የሚገባውን ሰው አየሁ፡ አንድ ታላቅ፡ ግዙፍ ሰው፡ በምሳሌያዊ አነጋገር መልኩ፡ አባቴን፡ የሚወክል ነበር። አንዲት ሴትም አየሁ፡ እሷም እናቴን አትመስልም፡ ነገር ግን፡ በዚያ ውስጥ፡ እናቴ ነበረች። ይህም ሰው (ይህ አባት ተብዬው፡ ማለት የሴቲቱ ባል) ሴቲቱን በጭካኔ እየበደላት ነበር፡ እና ትልቅ የእንጨት ጉቶ ይዞ ነበር፡ **እንደዚህ** አድርጎ ይይዛትና በዚህ በእንጨት ጉቶ ይመታታል፡ እርሷም ትወድቅና ወደ ታች ትወርዳለች። ከ—ከዚያ በኋላ፡ ከጊዜ በኋላ፡ ተመልሳ ትነሣለች። ዙሪያዋ ይራመዳል፡ እርሷን እንደገና ለመምታት ሃሳብ ያሰብና፡ እንደገና ይመታታል። ከሩቅ ቆሜ፡ እያየሁት ነበር።

16 በመጨረሻም፡ ግን የሚያደርገው ነገር መታገስ አቃተኝ። እኔም ከዚህ ሰው በጣም ያነሰኩ ነበርኩ፡ እንደ አባቴ ነገር ነበርና። እኔም ወደ እሱ ሄጄ ጣቴን ፊቱ ላይ ጠቁሜ። "እንደገና እንዳትመታት፡" አልኩት። አያችሁ? እንደዛ ሳደርግ፡ አንድ ነገር መሆን ጀመረ። እጆቼ መወጣጠር ጀመሩ፡ ከዚያ ግዙፍ፡ ጠንካራ ጡንቻዎችን አወጣሁ። እንደዚህ ዓይነት ጡንቻዎችን አይቼ አላውቅም። ሰውየውን አንቄው ያዝኩትና፡ እንዲህ አልኩት፡ "ሁለተኛ እንዳትመታት። በድጋሜ ከመታሃት፡ የምትጋፈጠው ከእኔ ጋር ነው" አልኩት። ሰውየውም ፈራኝና፡ ትቷት ሄደ። እኔም ከእንቅልፌ ነቃሁ።

17 እናሆ፡ በዚያ ተኝቼ ሳለሁ፡ ወዲያውኑ፡ በአፍታ ውስጥ፡ የህልሙ ትርጓሜ መጣ። ይህም፡ እርግጥ ነው፡ ይህች ሴት፡ በምሳሌያዊ አነጋገር፡ ቤተ ክርስቲያን ነች፡ ማለትም እንደ እናት ናት። በቤተክርስቲያን ላይ የበላይነት እንዳለው ሁሉ፡ ያየሁት አባት በእርሷ ላይ የበላይነት ነበረው፡ ልክ ባል በሚስት ላይ የበላይ እንደሆነ። ቤተክርስቲያንን እየደበደቧት ያሉት እነዚህ ሃይማኖታዊ ተቋሞች ናቸው፡ ልክ እንደዛ እግሯ ላይ እንድትቆም እንኳን አይፈቅዱላትም። እሷ ለመነሳት፡ ወይም አንድ ነገር ለማድረግ በምትሞክርበት ጊዜ ሁሉ፡ እነዚያ ሰዎች፡ የሃይማኖት ተቋም፡ ወደ ታች ይመቷታል። ጣቴን በፊቱ ላይ መጠቆሜን በመቀጠል—ይህ ማለት የእምነትን ጡንቻ አገኘሁ ማለት ነው፡ ስለዚህ "የምትጋፈጠው ከእኔ ጋር ነው፡ አየህ? " አልኩት። ምክንያቱም፡ እዚያ ውስጥ የእግዚአብሔር የሆኑ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ያም መልካም ነገር ነው። እ...

18 ለሁለት፡ ወይም ለሦስት፡ ሰዓት ያህል ነቅተን ነበር። ከነዚህም መካከል አንዷ የሆነችው፡ ሴት ልጄ፡ ርብቃ፡ በሉዊስቪል በሚገኘው፡ ሜቶዲስት ሆስፒታል ትሠራለች። ኦህ፡ ይህ፡ መደበኛ የሆነ የነርሲንግ ስልጠና ነው። "ካንዲይ ስትራይፐርስ፡" ወይም እንደዛ ያለ ነገር፡ ብለው ይጠሯችኋል። በ... ዚያ ጠዋት፡ እንድትመጣ ተጠተዋት ነበር፡ ያነቃኝም እሱ ነው። ጥዋት ነበር፡ እርሷም፡ ከትምህርት ቤት ጓደኞቿ ጋር፡ እ—እዚያው አንድ ላይ ይሰራሉ፡ ወደ

ሉዊስቪል ማድረስ ነበረብኝ። በአስር ሰዓት ላይ እዚያ መድረስ ነበረባቸውና። ሚስቴም ለምን ወደ መኝታ ክፍሏ መግባት እንዳልቻለች ጠየቀችኝ። ቆልፌው ነበርና።

19 አሁን፡ በሕይወቴ ብዙ ነገሮች አጋጥመውኛል፡ ነገር ግን እንዲህ ያለ ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም። ወደ ቅዠት ገባሁ። ትርጓሜውን አላውቅም። በሕይወቴ ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም። ነገር ግን፡ እየቆየሁ ስሄድ፡ ራዕይ መሆኑን እየተረዳሁ መጣሁ፡ በራዕዩ ውስጥም ነበርኩ። ነገር ግን ከልጄ ዮሴፍ ጋር፡ እየተነጋገርኩ ነበር። በዚያን ጊዜ፡ በክፍሉ ውስጥ አልነበረም። በሆነ መንገድ፡ ራዕዩ ሲያገኝኝ፡ ከዮሴፍ ጋር እየተናገርኩ ነበር።

20 ወ—ወደ ላይም ተመለከትኩ። በፒራሚድም ቅርጽ እየበረሩ፡ ግማሽ-ኢንች ያህል ርዝመት ያላቸው፡ ትንሽ፡ ትናንሽ ወፎች፡ ከፊቴ መጡ። አሰላለፋቸውም፡ ከላይ በላይኛው በኩል ያሉቱ፡ በ... በመጀመሪያው መስመር፡ ሦስት፡ ወይም አራት ነበሩ። ከዚያም፡ በቀጣይ፡ በሚቀጥለው መስመር ሰምንት ወይም አሰር ነበሩ። በመጨረሻው መስመር፡ አሰራ አምስት ወይም ሃያ ነበሩ።

21 እነርሱም ተዋጊዎች ነበሩ፡ ምክንያቱም ክንፎቻቸው የተወጋጉ ነበርና፡ የሆነ ነገር እያሉ፡ ከእኔ ጋር ለመነጋገር የሚሞክሩ ይመስላሉ። እኔም በምዕራብ ነበርኩ፡ በቱክሰን፡ አሪዞና አካባቢ ይመስለኛል። ወፎቹም ወደ ምሥራቅ ይመለከቱ ነበር። እኔም በቅርብ እያዳመጥኳቸው ነበር። የሆነ ነገር ለመናገር እየሞከሩ ነበር፡ ለእኔ የሆነ ነገር ለመንገር የሚሞክሩ ይመስላል። እነሱም ትንሽ ላባ ነበራቸው፡ ሁሉም ላባዎቻቸው የተመታቱ፡ ሌላም ነገር የሆኑ ናቸው። እነሱም በጦርነት እጅግ-የተጎዱ ነበሩ። ከዚያም፡ በድንገት **እንደዚህ** እየዘለሉ፡ አንዱ ወፍ የሌላውን ቦታ፡ መያዝ ይጀምራል። እነዚያም፡ ትናንሽ ወፎች በፍጥነት፡ ወደ ምሥራቅ በረሩ።

22 እነዚያም ከሄዱ በኋላ፡ የተዘረጋ ክንፍ ያላቸው፡ ርግብ የሚመስሉ፡ ትላልቅ ወፎች መጡ። በ—በቡድን ተ—ተሰብስበው መጡና፡ በፍጥነት፡ ከትናንሾቹ ወፎች የበለጠ ፈጥነው፡ ወደ ምሥራቅ በረሩ።

23 እና በእንቅልፍ ውስጥ እንደነበርኩ... ሁለቱ ንቃተ ህሊናዎቼ አንድ ላይ ሲሆኑ፡ በተመሳሳይ ሰአት እዚህ እንደቆምኩና፡ በሌላም ቦታ እንነበርኩ አውቃለሁ። አያችሁ? "አሁን፡ ይህ ራእይ ነው፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ግዴታ ማወቅ አለብኝ፡" ብዬ አሰብኩ።

24 ሁለተኛው የወፍ ቡድን እንዳለፈ፡ ወደ ምዕራብ ተመለከትኩ። በህይወቴ አይቻቸው የማላውቃቸው፡ ሃይለኛ አምስት መላእክት፡ ፒራሚድ በሚመስል መልክ፡ በእያንዳንዱ ጎን ሁለት ሁለት ሆነው አንዱ ከላይ ሆነው መጡ። እንዲህ ያለ አስደናቂ ፍጥነት፡ አይቼው አላውቅም። አንገቶቻቸውን ወደ ኋላ አድርገው፡ የተዘረጋውን ክንፎቻቸውን፡ በፊጥነት እያርገበገቡ ይመጣሉ! ሁሉን ቻይ የሆነው የእግዚአብሔር ኃይል፡ ከመሬት ላይ፡ ሙሉ በሙሉ፡ ወደላይ እስከሚያስነሳኝ፡ ድረስ በኃይል መታኝ።

ጆሴፍ አሁንም ሲናገር መስማት እችል ነበር።

25 ልክ የሚያስደነግጥ አይነት ድምጽ፡ ታላቅ የሆነ ነገድጓድ ድምጽ፡ ከ—ከርቀት ወደ ደቡብ በኩል፡ እየነጎደ ሄደ። እኔም ከመሬት ከፍ በተደረግኩ ጊዜ... መላእክቱ ፍጥነታቸው እጅግ የሚያስደነግጥ ነበር! እና አ—አሁን፡

እያችሁ፡ እ—እመጣጣቸው፡ **እንደዚያ** አይነት ቅርጽ ይዘው፡ ወደ እኔ አቅጣጫ እየተወነጨፉ አሁን እያቸዋለሁ።

26 አሁን፡ እያለምኩ አይደለም፡ አሁን። አይደለም። አሁን እዚህ በደምብ ነቅቼ እንዳለሁት፡ እዚያው ነበርኩ። እያችሁ?

27 ነገሩ ይኸው እንዲህ ሆነ። ወደ ላይ ሲያነሳኝ፡ እንዲህ ብዬ እስከማስብ ድረስ፡ በጣም ፈጣኖች ነበሩ... የሆነ ነገር እንደሚፈነዳ፡ እንደ፡ ከባድ ድምጽ ወጣና፡ ከባድ ፍንዳታ ሰማሁ። ይህ ሲሆን ደግሞ፡ "በቃ፡ በሆነ ነገር፡ ይኸው፡ በሆነ አይነት ፍንዳታ እሞታለሁ፡" ብዬ አሰብኩ። እ—እና እ... እነዚህን ነገሮችን ሳስብ፡ እንዲህ አሰብኩ፡ "አይ፡ እንደዚያ አይሆንም። ምክንያቱም፡ ፍንዳታ ቢሆን ኖሮ፡ ዮሴፍንም፡ ያገኘው ነበር። ምክንያት፡ እሱም አለ፡ አሁንም እዚያ እንዳለ፡ እያሰበ እየተናገረ ነው። እየሰማሁት ነበር። ያ አይደለም አልኩ።"

28 አሁን፡ ይህ ሁሉ አሁንም በራዕይ ውስጥ ነበር። እ... እያችሁ? በራዕይ ውስጥ ነበር።

29 ከዚያም፡ ልክ እንደተወሰድኩ ሰባንን፡ ሁሉም በአንዴ... በዙርያዬ ነበሩ። ላያቸው አልቻልኩም፡ ነገር ግን ወደ እነርሱ ወደ ፒራሚድ ኮንስታሌሽን ተወሰድኩኝ፡ ወደ አምስቱ፡ የ—የመላእክት ኮንስታሌሽን ወዳሉበት ገባሁ። "አሁን፡ እንደኛው የሞት መልአክ ይሆናል። አምስቱ ጸጋ ይሆናሉ፡" ብዬ አሰብኩ ነበር። እያልኩ እያሰብኩ ነበር። እንዲህ አሰብኩ፡ "ኦህ! መልእክቴን ይዘው—ይመጣሉ። ይህም ሁለተኛም ሰህበት ነው። ከጌታ ዘንድ መልእክት ሊያመጡልኝ መጥተዋል" ብዬ አሰብኩ። የቻልኩትን ያህል፡ በሙሉ ሀይሌ ጮህኩኝ፡ "ኢየሱስ ሆይ፡ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ? " እንደዛ ብዬ ስጮኽ፡ ራዕዩ ትቶኝ ሄ—ሄደ።

30 ከ—ከ—ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፡ ትክክል ሆኖ አልተሰማኝም። እያችሁ? ትላንትና ሙሉ ቀን፡ ቤት ውስጥ፡ መቆየት ነበረብኝ፡ ከራሴ ውጪ የሆነ ስሜት ሲሰማኝ ነበር። አእምሮዬን ነጻ ማድረግ አልቻልኩም። የጌታ ክብር እና ኃይል! ትቶኝ ሰሄድ፡ ደንዝዤ ነበር። እጆቼን ለማሸት እየሞከርኩ ነበር። "ትንፋሼን መቆጣጠር አቃተኝ፡" ብዬ አሰብኩ። በወለሉ፡ ወደፊትና ወደኋላ፡ ተመላለስኩ። አሰብኩ፡ "ጌታ ሆይ፡ ምን ማለት ነው? ምን ማለት ነው? " ከዚያም፡ ቆምኩኝ። እኔም፡ "አቤቱ አምላኬ ሆይ፡ እኔ ባሪያህ... እ—እኔ ምንም አልገባኝም። ለምን? ያ ምንድነው? ጌታ ሆይ፡ አስታውቀኝ።" በቃ፡ እ...

31 "የጌታ ኃይል፡" ሰላችሁ፡ ልነግራችሁ አልችልም። ያንን ለማስረዳት ምንም አይነት መንገድ የለም። እዚህ በረከቶች መካከል እንደሚሰማችሁ አይነት፡ አይደለም። እነዚያ የጌታ በረከቶች ናቸው። ይሄኛው የተቀደሰ ነው! ኦህ፡ ማይ! ሟች ሊገምተው እንኳን ከ—ከሚችለው ከማንኛውም ነገር በላይ ነው። እያችሁ? ያም በ—በጣም፡ አሰጨነቀኝ። ያ... በረከት አይደለም። ጭንቀት ነው። ትጨነቃላችሁ። እያችሁ? ያ ነው። ከቻላችሁ...

32 ሰሜቱ ምን አይነት እንደነበረ... ለሰዎች ምን እንደ ሆነ፡ ልነግራቸው የምችልበት መንገድ ባገኝ ኖሮ! እዚህ ተቀምጠን፡ መደሰትን እንደመፈለግ፡ አይደለም። በ—በውስጣችሁ ያለውን እያንዳንዱን ነርቭ የሚነካ... ከፍርሃት በላይ የሆነ ነገር ነው። ከመፍራት በላይ ነው። የተቀደሰ ክብር ነው። ለ... ለ... ማስረዳት የሚቻልበት ምንም መንገድ የለም። ጀርባዬ፡ ወደ ላይ-እና-ወደ ታች

አከርካሪ አጥንቴን፡ ጣቶቸን፡ ወደ ላይ-እና-ወደ እግሬንና የእግሬን ጣቶቼን፡ ሙሉ ጀርባዬ፡ እንኳ ሳይቀር፡ ሁለንተናዬ በሙሉ ደነዘዘ፡ አያችሁ፡ ልክ የ—የሆነ ቦታ፡ የሆነ አለም እንደሄዳችሁ ነው። እ—እናም ቀስ በቀስ፡ እየተወኝ መጣ፡ ጌታን እ—እንዲህ አልኩት፡ “አምላክ ሆይ፡ ታስታውቀኛለህን? ”

33 እንደማስበው፡ ከዚህ ጋር የሚቀራረብ፡ ጠንካራ የሆነ ነገር ያጋጠመኝ፡ ዙሪክ፡ ስዊዘርላንድ ሳለሁ ነበር፡ የጀርመን ንስር እንግሊዛዊው ፈረስ-ጋላቢ በአፍሪካ በኩል ሲወርድ ስመለከተው አሳይቶኝ ነበር። እርሱም፡ “ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል ክብርንም ጐድሎአቸዋል” አለ።

34 እንዲረዳኝም ወደ እግዚአብሔር፡ ሰጮኽ ነበር። ት—ትርጉሙን እንዲሰጠኝ ፈልግሁ፡ ምክንያቱም ይህ ማለት የ—የኔ መሄድ ከሆነ፡ የምገደል ከሆነ ለማወቅ ፈልጌ ነበር። የምሞት ከሆነ፡ ጉዳዩን ለቤተሰቤ ምንም አልነግራቸውም። ወደ ቤት የምሄድበት ጊዜዬ ነው፡ ለምን፡ ወደ ቤት እሄዳለሁ፡ ያ ነው በቃ። ነገር ግን እ—እንደዛ ከሆነ፡ ለቤተሰቤ ምንም መንገር አልፈልግም፡ ስለሱ ምንም እንዲያውቁ አልፈልግም። እንደዚያ እንዲሆን መተው ነው፡ ያ—ያ ነው በቃ።

35 እኔም፡ “ጌታ ሆይ፡ እርዳኝ፡ ለቤተሰብ መንገር አልፈልግም፡ ወ—ወደ ሰማይ ቤቴ፡ የ... የምትጠራኝ ከሆነ፡ እሺ፡ እ—እሄዳለው” አልኩ። አያችሁ። እንዲህ አልኩ... እና፡ እናንተ፡ እንደ...

36 እናንተም “ደህና፡ በራእይ የተናገርከውን፡ ራእዩ የሚናገረውን ስለ ምን አታስብም፡” ትጠይቁኛላችሁ?

37 ነገር ግን ያኔ እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ማሰብ አትችሉም። ለ... ለማነኛውም፡ አልቻልኩም። በአሳቤም... ተቸገርኩ፡ ተበሳጨሁ። እንዴት ማሰብ እንዳለባችሁ አታውቁም። ማሰብ አትችሉም።

38 እንዲህም አልኩ፡ “የሰማይ አባት ሆይ፡ ያ ማለት—ፍንዳታው ይገድለኛል ማለት ከሆነ፡ ደህና፡ አሁን አሳውቀኝ፡ ስለዚህ ነገር ምንም አልናገርም። ክብርህና ኃይልህ በላዬ እንደገና ይምጣና፡ እንደገና ያንሳኝ። ወይም፡ ክብርህና ኃይልህ በላዬ እንደገና ይምጣና፡ ከዚያም ያ—ያ ማለት ትወስደኛለህ ማለት እ—እንደሆነ አውቃለሁ፡ ስለዚህም ለራሴ ብቻ እይዘዋለሁ” አልኩ። ምንም አልሆነም።

39 ስለዚህም እንዲህ አልኩ፡ “እንግዲህ፡ ጌታ ሆይ፡ መልእክተኞችህን ለተልዕኮዬ የምትልክ ከሆነ፡ ኃይልህ እንደ ገና ይምጣ” አልሁ። ልክ ከክፍል እንዳወጣኝ ይመስላል!

40 ቢሆንም፡ መጽሐፍ ቅዱሴን በእጄ እንዳለ፡ ወ—ወደ ራሴ ተመለስኩ፡ ከዚያ፡ አያችሁ፡ እግዚአብሔርንም እንዲረዳኝ ጠየቅሁ። በጠየኩትም ጊዜ፡ እዚያው፡ ከ—ከዛ ጋር የሚያያዝ ነገር፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ነገር አሳየኝ። “በእውነቱ ያ ሊሆን ይችላልን? ይህ እንዴት ያደረኩት፡” ጥያቄ ተፈጠረብኝ? እናም፡ ኦህ፡ እነዚህን ነገሮች ማብራራት አ—አልችልም፡ ሰዎች። ከማውቀው ነገር በላይ ነው። አያችሁ?

41 ሚስቴ በጣም ለየት ያለች ሴት ናት፡ በአለም ላይ ካሉ ምርጥ ልዩ ሴቶች አንዷ ነች። ነገ ግን፡ ለተወሰነ ሰአት፡ ስለሆነው ነገር ምንም አልተናገርኩም።

ቀጠልኩ። የሆነ ነገር እንደተፈጠረ ታውቃለች። ስነግራትም፡ እንዲህ አለች፡ “ታውቃለህ፡ ቢል፡ በእነዚህ ብዙ ነገሮች፡ አይቼሃለሁ፡ ሰምቼሃለሁ። “በፍፁም ልቤ እንዳምንህ ታውቃለህ፡” አለችኝ፡ እንዲህ አለች፡ “ይህ በእርግጥ የሆነ ነገር አለው፡” አለች።

42 የእነዚያ አምስቱ መላእክት በአንድ ላይ፡ በህብረ መልክ፡ በፍንዳታና በፍጥነት በዚያ መልኩ፡ መምጣታቸው፡ እ—እንቀጠቀጠኝ። ልክ፡ ያ—ያንን ፒራሚድ እዚህ ሰየዋለው፡ አያችሁ፡ መጀመሪያ፡ የመሰሉት፡ በ… በርቀት ሲታዩ፡ ያንን የርግብ ቀለም አይነት፡ ይመስላሉ። እ—እነርሱም **በዚህ** አቅጣጫ ነው የመጡት። እነርሱም፡ አንድ፡ ሁለት፡ ይመስላሉ፡ ሦስት፡ አራት፣ ከዚያ አንዱ ከላይ በኩል፡ አያችሁ፡ አምስት ይፈጥራሉ። እንደዚህ ባለ ፍጥነት ይመጣሉ! ምንም ነገር፡ ጄቶች፡ ምንም ሌላ ነገር **ከፍጥነታቸው** ጋር ሊወዳደር አይችልም።

43 በትክክል አይቻቸዋለሁ፡ ጭንቅላታቸው ወደ-ጎን ዞሯል። ክንፎቻቸው ወደ ኋላ ተዘርግተዋል፡ ሙሉ-በሙሉ ታጥቀዋል፡ እነሆ መጡ፡ “ዊህው!” ልክ **እንደዛ**። ልክ ወደ ታች ወረዱና፡ ወደዚህ ወደሰሩት የሕብረት ፒራሚድ ውስጥ አስገቡኝ። ጠፍቼ፡ ከመሬት ተነስቼ አይቻለሁ። ምናልባት በ… በርቀት፡ “ሁምም፡” የሚል ድምጽ፡ የሰማሁ መሰለኝ! ልክ እ—እ—አውሮፕላን የድምፅ ገደብን ሲያልፍ የሚያሰማውን አይነት ድምጽ፡ እንደዛ ሲሆን ሰምታችኋል፡ በርቀት የሚሰማ የሚንጎዳጎድ ድምጽ።

44 እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “እንደዚህ የሚመስለኝ ምናልባት ለአሁን ብቻ ነው፡ ይህ ራዕይ ትቶኝ ሲሄድ፡ በፍንዳታ ወይም በሌላ ነገር ልገደል ነው ማለት ሊሆን ይችላል” ብዬ አሰብኩ። እኔም፡ “እነሆ እዚህ ነኝ። ወደ ላይ ተነስቻያለው። እ… እነዚህም፡ በሆነ ሰፍራ ይኸው አሉ፡ እ—እኔም በዚህ ውስጥ ነኝ፡ በዚህ የመላዕክት ፒራሚድ ውስጥ ገብቻለሁ። ነገር ግን፡ እ—አላውቅም። ምናልባት ጌታ ወደ ቤት ሊወሰደኝ ይመጣል።”

በዚያም ዮሴፍ፡ “አባዬ? ” ሲለኝ ሰማሁትና፡

“አይ፡ ያ ከሆነማ፡ እሱንም፡ ይወሰደው ነበር፡” ብዬ አሰብኩ።

45 ከዛ የሆነ ነገር እንዲህ አለ፡ “አንተ… ” አስታውሱ፡ የሆነ ነገር፡ ሁል ጊዜ የምጠብቀውን መልእክት፡ እየጠበቅኩ ነው።

46 በቀደምለት፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ያየሁት ራእይ፡ ከፀሐይ እስከ፡ ወደዚህ ሰፍራ፡ እንዴት እንደምሰብክ፡ ሰለሚሆነው ነገር እንዴት እንደምሰብክ፡ እየነገረኝ እንደነበረ ታውቃላችሁ። ከዚያም—እንዲህ አለ፡ “አሁን አስታውስ፡ ሁለተኛው ጠርዝ ገና ይመጣል።”

“መልእክት ይኖራል፡” ብዬ አሰብኩ።

47 እዚህ መልእክቴን ታስታውሱታላችሁ? የመደምደሚያው አለት መከፈት፡ ማለት፡ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያልተጻፉ ሰለ ሰባቱ ድምፆችንና ማህተሞች ያትታል። አስታወሳችሁ? ወደዚያ ወደ ፒራሚዱ ወሰደኝ።

48 ጁኒ ጃክሰን፡ እዚህ ከሆንክ፡ ከረጅም ጊዜ በፊት የነገርከኝ ህልም አለ። ዛሬ ጠዋት አልናገርም። እግዚአብሔር… ፍጹም ነው። የህልሙን

ፍቺውን ስላልነገርኩህ ይቅርታ አድርግልኝ፡ ምክንያቱም፡ የሆነ ነገር ሲንቀሳቀስ አይቻለሁ።

እንዲሁም ጄ. ቲ.፡ ተመሳሳይ ነገር፡ አያችሁ። እና አ—አ—አውቄው ነበር።

እንዲሁም እህት ኮሊንስ፡ ተመሣሣይ ነገር ነው። አያችሁ?

እና ስድስቱም፡ በቀጥታ ተመሳሳይ ነገር ያስረዳሉ።

49 ከአመታት በፊት፡ ለሁላችሁም የነገርኳችሁ ራእይ፡ በቀደም ተፈጽሟል። አያችሁ? ሆኗል።

50 ነገሩ ይኸው፡ ሁሉም ነገር፡ በግልጽ ይታያል። የሆነ ነገር እየተንቀሳቀሰ ነው። ምን እንደሆነ አላውቅም። እግዚአብሔር ይርዳኝ፥ ጸሎቴ ነው።

እንጸልይ።

51 የሰማይ አባት ሆይ፡ ሟቾች ብ—ብቻ ነን፡ በጠዋቱም እዚህ ቆመናል። ጌታ ሆይ፡ ይ... ይህን ታናሽ መንጋና፡ ይህችን ቤተ ክርስቲያን እንድመራ ልከኸኛል። እኔም ፍጻሜዬ ላይ ደርሻለሁ። የትኛው መንገድ፡ ምን፡ የት፡ ምን እንደሚመጣ አላውቅም። ነገር ግን ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ፡ አንተን ለሚወዱት፡ “ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚደረግ” እንዲሁም እንደ ሃሳብህ ለተጠሩት። እግዚአብሔር ሆይ፡ ታላቅ የምሕረት እጅህ በእኛ ላይ ትሆን ዘንድ፡ እለምንሃለሁ።

52 አንተ አምላክ እንደ ሆንህ በእውነት እናውቃለን። አንተ በጥንት ዘመን ኖረህ ያለፍክ እንዳልሆንህ፡ ነገር ግን ዛሬም እንደምትኖር እናውቃለን። አንተ ሁሌም አምላክ ነበርክ። ሁሌም አምላክ ትሆናለህ። አንተ ከዘመናት በፊት አምላክ ነበርክ፡ ጊዜ ሲጠፋም አምላክ ትሆናለህ። አሁንም አምላክ ትሆናለህ።

53 አቤቱ ጌታ ሆይ፡ በእጆችህ ላይ ነን። እኛ ጭቃ ብቻ ነን፡ አንተ የምታበጀን፡ ሸክላ ሠሪ ነህ። ጌታ ሆይ፡ አንተን ለማክበር ከሁሉ የተሻለውን አገልግሎት እንድናገለግልህ በሚያስችለን መንገድ፡ ህይወታችንን ቅረጸው። ይሁንልን፡ አባት ሆይ። በእጆችህ ውስጥ ነንና።

54 ራሳችንን ወደዚህ ለማምጣት ምንም መንገድ አልነበረንም፡ ወይም እንዴት እንደምንወጣ እናውቅም። ጌታ ሆይ፡ አንተ ሕይወትን ሰጠን፡ አንተም... እኛም ህይወታችንን፡ ለአንተ እንሰጣለን፡ ስለዚህም፡ አንተም በምላሹ፡ የዘላለም ሕይወትን፡ ሰጠን። እምነታችን ይህን ነገር በውስጣችን ይተነፍሳል። በዚህም ምክንያት እንወድሀለን፡ ምክንያቱም አንድ ቀን እንደምናይህ እናውቃለን፡ አንተም በክብርህ ውስጥ ትሆናለህ። ወደ እርሱ እንመለከታለን። እነዚህን ቃላት ለመስማትም እንናፍቃለንና፡ “መልካም እና ታማኝ ባርያዬ፡ መልካም አድርገሃል። ዓለም ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ ወደተዘጋጀላችሁ፡ ወደ ጌታ ደስታ ግቡ።” አምላክ ሆይ፡ ሁላችንም ሰንገናኝ፡ እስከዚያው ጊዜ ድረስ፡ ምራን።

ባሪያዎችህ ነን፡ ለኃጢአታችንም ይቅርታ እንጠይቃለን።

55 ጌታ ሆይ፡ እነዚህ ታላላቅ ራዕዮች፡ ለባርያህ ከአቅም በላይ ናቸው። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። እኔ ራዕዮቹ እ—እንደሚመጡ ብቻ አውቃለሁ። ምን እንደተባለ፡ ያየሁትን ነገር ብቻ መናገር እችላለሁ። ጌታ ሆይ፡ አንዳንድ ጊዜ ያስፈራኛል። ምን ማድረግ እንዳለብኝ—ም ራሴን እጠይቃለሁ።

56 ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስን እወስድና ኢሳይያስ በዚያ ቀን በቤተ መቅደሱ ውስጥ፡ እነዚያን መላእክት ሲመለከት፡ ምን ተሰምቶት ሊሆን እንደሚችል አነባለሁ። "የእግዚአብሔርን ክብር በዓይኔ አይቻለሁና፡ ወዮልኝ!" ማለቱ ምንም አያስደንቅም።

57 ነብዩ በታላቅ ድምጽ ያለቀሰው፦ በቤተ መቅደሱ ውስጥ መንጻትን ካገኘ በኋላ፡ መልአኩም ፍምን በጉጤጥ ወስዶ ከንፈሮቹ ላይ ባደረገለት ጊዜ፡ ከንፈሩ የረከሰበትና፡ በረከሱ ሰዎች ዘንድ፡ አብሮ የሚኖር ሰው መሆኑን ከተናዘዘ በኋላ ነው። በዚህ ሁሉ ግን፡ ነብይ ነበር። መልአኩም ፍምን በጉጤጥ ወስዶ ከንፈሮቹን ዳሰሰውና አነጻው፡ እንዲህም አለው፡ "አሁን ሂድና፡ ትንቢት ተናገር።"

ጌታ አምላኬ ሆይ፡ ኢሳይያስም፡ "እነሆ፡ ጌታ ሆይ። እኔን ላከኝ" ብሎ ጮኸ።

58 እሱም፡ ስለዚህ ክፉና አመንዝራ ትውልድ፡ "ማን ይሄድልናል? " ባለ ጊዜ ነበር!

59 አምላክ ሆይ፡ እንደገና ድገመው። እንደገና ይምጣ፡ አምላክ ሆይ። መንፈስ ቅዱስ ከሚያነጻው እሳት ጋር ላክልን። ርኩስ ከንፈር፡ እንዳለኝና፡ ከረከሱ ሰዎች ጋር በዚህች ምድር እንደምኖር፡ እናዘዛለሁና። በአንተ ፊት የረከሱ ነን፡ ጌታ ሆይ። ነገር ግን፡ አቤቱ፡ የሚያነጻውን ኃይል፡ መንፈስ ቅዱስን ላክ! ጌታ ሆይ፡ አጽዳን። አቤቱ ባሪያህን፡ ቀድስ።

60 ከዚያም፡ ጌታ ሆይ ተናገር። ባሪያህ ያዳምጣል። ያንን ድምፅ ለመስማት እጓጓለሁ። የአንተ ነኝና። በመሠዊያህ ላይ፡ ራሴን አቅርቤ እያለሁ፡ እንደፈለግህ ተጠቀመኝ፡ ጌታ ሆይ። ጌታ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስ ይቀድሰኝ፥ ጌታ ሆይ፡ አንድ ሰው እንዲሄድልህ ከፈለግህ፡ ጊዜውና ሰዓቱ አሁን ከሆነ፡ ቀብተህ ላከኝ።

61 እ—አላውቅም፡ ጌታ ሆይ። እ—እነዚያን መላእክት እንዳየሁ ብቻ አውቃለው። እነዚያ ነገሮች በትክክል እውነት መሆናቸውን አንተ ታውቃለህ። እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ "ወዮልኝ፡" ስለዚህ እግዘኝ።

62 አሁንም ይህን ህዝብ ባርከው። ዛሬም የጌታችን የልዴት በአል ከማክበራችን በፊት፡ በዋዜማው እዚህ ተገኝተናል። እንድትረዳን ዘንድ እንጸልያለን።

63 በዚህ ጠዋት፡ ባርያህ፡ ወንድማችን ነቪል፡ ምናልባት ትንሽ እረፍት ማድረግ እንዳለበትና፡ እኔ መሰበክ እንዳለብኝ ተሰምቶታል። እ—አሁንም እንድትረዳኝ እጸልያለው።

64 ጌታ ሆይ፡ እዚህ ያሉት ሁሉ፡ እኛ ሁላችንም፡ አንተን እንፈልግሃለን። ለጥቂት ጊዜ ቃልህን ስናነብና ስናሰላስለው እንድትባርከን እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ መንፈስህ በእኛ ላይ ይምጣ። እየሞተ ያለውን ዓለም ለማናወጥ፡ ታላቁ የዘላለም አምላክ ከመምጣቱ በፊት፡ ከመሠዊያው በሚመጣ፡ በእግዚአብሔር መልእክት፡ በመንፈስ ቅዱስ አንጽተህ፡ በእሳቱ አቀጣጥለን። በውድ ልጁና፡ በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

65 አሁን ትኩረታችሁን ወደ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና፡ ወደ ያዝኳቸው ጥቂት ማስታወሻዎች፡ ልመልሳችሁ እወዳለሁ።

66 ዶክ፡ ወይም ቢሊ፡ ወይም ከነሱ አንዱ፡ ይመስለኛል፡ እንደነገረኝ፡ ለልጆቹ ሲባል፡ ትንሽ ቀደም ብለው መውጣት እንደሚፈልጉ ነግረውኛል። ለልጆች የተወሰነ ሰጦታ አዘጋጅተዋል።

67 እናንተ ከሰንበት ትምህርት ቤት የወጣችሁ ልጆች፡ ት—ትንሽ ቈይታ አድርጉ፡ ትንሽ ብቻ ጠብቁ። እዚህ የምንናገረው ነገር ትንሽ ጥልቅ ሊሆንባችሁ ይችላል፡ ለ—ለጥቂት ደቂቃ ግን ከእናታችሁና ከአባታችሁ ጋር፡ ቁጭ በሉ። ለእነርሱ መናገር እፈልጋለሁ።

68 አሁን፡ በመዝሙረ ዳዊት፡ ከመዝሙር 89 እናነባለን፡ ከመዝሙር 89 ላይ፡ አንድ ሁለት ጥቅሶችን ማንበብ እፈልጋለሁ። ከመዝሙር 89 ላይ 50ኛ፡ 51ኛና፡ 52ኛ ቁጥር ለማንበብ እሞክራለሁ።

69 አሁን፡ ከኋላ ያላችሁ ሁሉ፡ በደምብ ይሰማችኋል? መሰማት ከቻላችሁ፡ እጆቻችሁን አንሱ። ስለዚህ የ... የትኛው ይሻላል... ሁሉም ማይኮች ይሰራሉ? [አንድ ወንድም፡ "እኔ እንጃ" አለ።—አርታዒ።] **ይህ** ይሻላል፡ ወይስ **ይህ**? **ይሄኛውስ**? **ይሄኛውስ**? ["በጎን ያሉት ሁለቱ ይሰራሉ።"] እዚህጋ፡ **እነዚህ** ሁለት በጎን ያሉት? ["**ይሄኛው፡ ይሄኛው፡** እና **ይሄኛው**።"] እሺ።

70 ይህንን በቴፕ ይቀዱት ይሁን አይሁን አላውቅም። ዛሬ ጠዋት ድንገተኛ ፕሮግራም ነው።

71 ነገር ግን አሁን፡ ጓደኞቻችሁን ማምጣት አትርሱ። በ—በሚቀጥለው እሁድ ስብሰባ ላይ፡ መገኘታችሁን፡ እርግጠኞች እንድትሆኑ እፈልጋለው።

72 ቤተክርስቲያኑ በቅርቡ ይጠናቀቃል፡ ብዬ እገምታለሁ። የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ሰባቱን ማህተሞች ለመስብከ፡ ተ—ተመልሼ እመጣለሁ።

73 በመዝሙር መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 89 ላይ፡ ከቁጥር 50 ጀምሮ እናነባለን። የእግዚአብሔርን ቃል ሲነበብ በጥሞና አዳምጡ።

> **አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ የባሪያዎችህን መነቀፍ አሰብ፡ የታላላቅ ሰዎች ነቀፌታ በብብቴ ተሸከምሁ፥**
>
> **አቤቱ ጌታ ሆይ፡ ጠላቶችህን የነቀፋትን፥ የቀባኸውን አካሄዱንም የነቀፋትን አሰብ።**
>
> **እግዚአብሔር ለዘላለም ይባረክ። አሜን፡ አሜን።**

74 ለጥቂት ደቂቃዎች ልናገራችሁ እፈልጋለሁ... በመጀመሪያ፡ ያንን እንዲታሰተውሉ እፈልጋለሁ፡ ያንን በጥንቃቄ፡ ደጋግማችሁ ደጋግማችሁ አንብቡት። ምናልባት አሁን በድጋሜ ብናነብ ይጠቅመናል። አሁን በደምብ አዳምጡ። አያችሁ?

> **አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ የባሪያዎችህን መነቀፍ አሰብ፡ የታላላቅ ሰዎች ነቀፌታ በብብቴ ተሸከምሁ፥**
>
> **አቤቱ ጌታ ሆይ፡ ጠላቶችህን የነቀፋትን፥ የቀባኸውን አካሄዱንም የነቀፋትን አሰብ።**
>
> **እግዚአብሔር ለዘላለም ይባረክ። አሜን፡ አሜን።**

75 ዳዊት እንደተናገረው፡ በደምብ አጥኑት። መጠቀም የሚፈልገው ርዕሰ… የገና ርዕሰ እንደገና መውሰድ፡ በጣም ያልተለመደ ነው፥ ነገር ግን ባለፈው እሁድ ባልተለመደ ርዕሰ ላይ ሰብክያለው። ርዕሱ ምን እንደነበረ አሁን ረሳሁት። ርዕሱ… [አንድ ወንድም፡ "**እየወደቀ ያለው ዓለም**" አለ።—አርታዒ።] ይቅርታ ምን አልከኝ? ["**እየወደቀ ያለው ዓለም**።"] እየወደቀ፥ **እየወደቀ ያለው ዓለም**።

76 አሁን ለዛሬ እሑድ፡ የምጠቀመው ርዕስ፡ **ስለ እግዚአብሔር ቃል መነቀፍ**። አሁን ደግሜ ልንገራችሁ፡ በጣም ጥሩ። ሰ… **ስለ እግዚአብሔር ቃል መነቀፍ**።

77 እግዚአብሔር ቃሉን የሚፈጽምበት፡ ጊዜና፡ ምክንያት አለው። እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ በትክክል ያውቃል። እኛ አናውቅም። እርሱ እንደሰጠን መቀበል አለብን። ነገር ግን፡ እርሱ ያውቃል፡ እ—እርሱ ለማድረግ ያቀደው ነገር ምንም ስሕተት አይኖረውም። ሁሉም ነገር ሊሆን የሚገባ ነገር ነው። አንዳንድ ጊዜ፡ የአንድን ነገር እውነተኛ የተፈጥሮ፡ እና ውበቱን ለማምጣት፡ ጠንካራና ከባድ ነገሮች፡ ሊኖሩ ይገባል።

78 ታውቃላችሁ፡ ዝናብ የሚወለደው ወጣ ገባ ባለው፡ አንድ አይነት ባልሆነ ደመና፡ በመብረቅ በተሞላ፡ በነጎድጓድ በተሞላ ሰማይ ውስጥ ነው። ዝናብ ባይኖር ኖሮ፡ አንኖርም ነበር። ነገር ግን ዝናብ ለማምጣት ምን እንደሚያስፈልግ አያችሁ? ነጐድጓድ፡ መብረቅ፡ ብልጭታ፡ ቁጣ። ከዚያ ውስጥ ዝናብ ይመጣል።

79 አዲስ ሕይወት ለማምጣት፡ አንድ ዘር መሞት፡ መበስበስ፡ መበላሸተ፡ መሸተትና፡ ወደ አፈር መመለስ አለበት።

80 ወርቅ ለማግኘት፡ ወርቁን ገልብጠው፡ ወደ ፊትና ወደ ኋላ በማድረግ፡ ቆሻሻው በሙሉ እስኪወገድ ድረስ መደብደብን ይጠይቃል። ስለሚያብረቀርቅ አይደለም፡ ምክንያቱም የብረት ፒራይት፡ ፉልስ ጎልድ በመባል የሚታወቀው፡ እንደ እውነተኛ ወርቅ ያብረቀርቃል። ነገር ግን፡ ሁለቱን… በተለያዬ ቦታ በተናጠል ካያችሁ፡ ለይታችሁ ልታውቋቸው አትችሉም፡ ነገር ግን አንድ ላይ ካስቀመጣችኋቸው፡ ለይታችሁ ልታውቋቸው ትችላላችሁ። ወርቁን የሚያጠራው ሰውዬ በ—በወርቁ ውስጥ የራሱን ምስል እስከሚያይ ድረስ መደብደቡ ይቀጥላል።

81 እግዚአብሔርም ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ጊዜና ዓላማ አለው። ጌታን ለሚወዱና እንደ ሃሳቡ ለተጠሩት በአጋጣሚ የሚሆን ነገር የለም። አያችሁ? አሰቀድመን ተወሰነናል። ምክንያቱም እርሱ ሊዋሽ ሰለማይችል፡ ሁሉም ነገር፡ በትክክል ይሰራል። እርሱም እንዲህ አለ፡ ለሁሉም ነገር ጊዜ፡ ወቅትና፡ የራሱ መንገድ አለው። እግዚአብሔርም በእያንዳንዱ ነገር በሰተጀርባ ላይ አለ። አንዳንድ ጊዜ ነገር ሁሉ በትክክል እየሄደ አይደለም ብላችሁ ታሰባላችሁ። በእኛ ላይ ነው። ፈተናዎችና ግራመጋባቶች፡ በእኛ ላይ ናቸው። ይህም በሚሆነው ነገር ሁሉ ላይ ምን ምላሽ እንደምንሰጥ ለማየት፡ እየተፈተንን ነው።

82 ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ቨርሞንት ውስጥ፡ እኔና ወንድም ፍሬድ፡ ከቻምፕሌይን ሐይቅ አቋርጠን፡ ወደ ኒው ዮርክ በኩል ደረሰን። እኔም ሳዲን ወደነበረበት፡ ወደ ሃሪከን ተራራ፡ ወደዚያ ተራራ ወጣሁ። እዚያ ጠፍቼ፡

ጌታ በዚያ ሁሉ አውሎ ንፋስ ውስጥ፡ እንዴት በመንፈስ ቅዱስ ብቻ፡ መርቶኝ እንዳወጣኝ አስታውሳለሁ። ጌታ ባያድነኝ ኖሮ፡ ሞቼ፡ እና ጠፍቼ ነበር፡ እዚያ በትንሹ ካምፕ ወስጥ የነበሩት፡ ሚስቴና ቢሊም ይሞቱ ነበር። እና እኔ ወደ ኋላ ተመለስኩ።

83 በፀደይ ወቅት፡ ወደ ካምፕ ለመግባት፡ በሄድን ጊዜ ትንሽ በረዶ ነበር። እዚያም ቆሜ ከወንድም ፍሬድ ጋር እየተነጋገርኩ ነበር፡ መንፈስ ቅዱስም እንዲህ አለኝ፡ “ብቻህን ተለይ” አለኝ። እኔም ለጥቂት ጊዜ ወደ ቁጥቋጦ ወዳለበት፡ ፈቀቅ አልኩ፡ እርሱም እንዲህ አለኝ፡ “አንድ ወጥመድ ተዘጋጅቶልሃል። አሁን ተጠንቀቅ” አለኝ። ነገር ግን እንዴትና፡ ምን እንደሆነ አልነገረኝም። ተመልሼ በመምጣት ለወንድም ፍሬድ ነገርኩት።

84 በዚያው ምሽት ወደ ቤተክርስቲያን ሄጄ፡ ለሰዎች አስታወቅኋቸው። በሚቀጥለውም ምሽትም ነገሩ ተፈጸመ። እዚያም ቆሜ ሳለሁ፡ ስለ አንዳንድ ፌዘኞች ሲነግረኝ፡ እንዲህ አለኝ፡ “በእጅህ ውስጥ ናቸው። የፈለከውን አድርግባቸው። አንተ ይሁን የምትለው ሁሉ፡ አሁን ይሆናል።”

85 ይኸውላችሁ። አንዳንድ፡ አክብሮት የጐደላቸው፡ እግዚአብሔርን የማይፈሩ፡ አንድ ወጣት ወንድ እና ወጣት ሴት፡ ስብሰባው ላይ ሲያሾፉ እና ሲያፌዙ ነበር። እኔ እየሰበክሁ ሳለሁ፡ ሕንጻ ውስጥ ከእሷ ጋር የብልግና ፍቅር-ለማድረግ እየሞከረ ነበር፡ የሁሉንም ሰው ትኩረት ለመሳብ እየሞከረ ነበር። ጭንቅላቷን ወደ ኋላ ጎተተና፡ በጭኗ ላይ ወጣና ሊስማት ሞከረ፡ በስብሰባው ውስጥ እንደዚያ እያደረጉ፡ ትኩረትን እየሳቡ ነበር።

86 መንፈስ ቅዱስም፡ “አሁን... በእጅህ ውስጥ ናቸው። ምን ታደርጋቸዋለህ” አለኝ?

87 ጥልቅ የሆነ ጸጥታ ሰፈነ። ሁሉም ሰው ጸጥ ብሎ ቁጭ አለ። እኔም፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ ምን ላድርግ” ብዬ አሰብኩ?

88 ከዚያ ትዝ አለኝ፡ ከሁለት ቀን በፊት የመንፈስ ቅዱስ ባያስጠነቅቀኝ ኖሮ፡ ሌላ ነገር ነበር የሚሆነው። “ይቅር እልሃለሁ፡” አልኩት። አሁን፡ እንድለው የፈለገው ይህ ነበር። አያችሁ?

89 ምክንያቱም፡ ምንም ቢሆን፡ እ—እኔም ኃጢአተኛ ሆኜ ኖሬአለሁና፡ ምናልባት በዚያ አይደለም፡ ይሁን እንጂ ኃጢአተኛ ነኝ። “በትንሹ ጥፋት ማጥፋት በሁሉም እንደማጥፋት ነው።”

90 ስለዚህ “ይቅር እላችኋለሁ፡” አልኳቸው። አሁን በዚያን ጊዜ የነበሩ፡ እዚህ የተቀመጡ ምስክሮች አሉ። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ መጣ።

91 አሁን፡ አያችሁ፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ትርጉም እንዳላቸው አምናለሁ። ስልጣን ምን ታደርጉበታላችሁ? የአንድ ድርጊት ግብረመልስ፡ እንዴት፡ ታዩታላችሁ? አንድ ነገር ድርጊት ሆኖ ከመጣ፡ ከዚያ ለዚያ ድርጊት እንዴት ነው ምላሽ የምትሰጡት? ምን ማለቴ እንደሆነ ተረድታችኋል? እናንተስ ምን ታደርጉ ነበር? ምናልባት ይህ ሁሉ አሁን ወዳለንበት ሁኔታ አድርሶናል። አላውቅም። ም—ምንም ማለት አልችልም። ግን ሁልጊዜ የሆነ መንገድ አለ...

92 አስታውሱ፡ የ—የቃሉ ነቀፌታ... ቃሉ ሁል ጊዜ ነቀፌታን ተሸካሚ ነው። በዘመናት ሁሉ፡ የተቀባው የእግዚአብሔር ቃል ሲነቀፍ ቆይቷል። ይህን መረዳት

ለማይችሉ ሰዎች እጅግ የሚከብዳቸው ለዚህ ነው፡ ይህንን ነቀፌታ እንዴት መቀበል እንዳለባቸው ማወቅ በጣም ይከብዳቸዋል።

93 የእግዚአብሔርን ስም የሚያስነቅፉ ነገሮችን በፅናት ተቋቁመው ብቁ እንደሆኑ በማሰብ በደስታ የተመለሱትን ደቀ መዛሙርት ታስታውሷቸዋላችሁ? እንዲህ ብሏል፡ "በክርስቶስ እግዚአብሔርን በመምሰል የሚኖሩ ሁሉ መከራ ይደርስባቸዋል፡" የቃሉ ነቀፌታ።

94 ፈተናውን ለማለፍ፡ ለማየት ሁሌም ይህንን ነቀፌታ መቋቋም አለባችሁ። ወደ ክርስቶስ የሚመጣ ማንኛውም ሰው መጀመሪያ እግዚአብሔር ለ—ለሾመበት ዓላማ፡ እንደ-ልጅ ሊሰለጥን ይገባል። አስታውሱ፡ ዝም ማለት የሚትችሉ ከሆነ! አስታውሱ፡ ለዚህ የጠራችሁ እርሱ ከሆነ፡ ይህ እንዳይሆን ሊያግደው የሚችል ምንም ነገር የለም። ምንም ያህል የሚያሰቃዩ ዲያብሎሶች ቢኖሩም፡ ይህ ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ቃል ይገለጥበት ዘንድ ነው። የተወለዳችሁት ለአንድ ዓላማ ሲሆን፡ ማንም ሰው ስፍራችሁን ሊተካ አይችልም። አስመሳዮች እና ሌሎችም ሁሉ ሊኖሩ ይችላሉ፡ ነገር ግን ስፍራችሁን በጭራሽ አይተኩትም። በትክክል። የእግዚአብሔር ቃል ድል ያደርጋል። ሊወድቅ አይችልም። እያንዳንዱ ክርስቲያን ይህን በማወቅ፡ መቆም የ—የሚገባው በዚህ ላይ ነው። ፈተናዎች ይመጣሉ፡ በሁሉም መንገድ፡ ከባድ ይመስላችኋል። ነገር ግን አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ዓላማ አለው፡ ሁሉንም ነገር ትክክል ይሆናል።

95 አሁን የእግዚአብሔር ቃል ፍጻሜውን ያገኘባቸውን አ—አንዳንድ ክንውኖችን እናስታውስ፡ በዘመናቸው የቃሉን አደራ የተቀበሉትን እንመልከታቸው።

96 በ—በቅርብ ጊዜ፡ አንድ ሰው እየነቀፈኝ መሆኑን፡ በመንፈስ ተሰማኝ። በቴፕ ስርጭት ውስጥ ሊሆን ይችላል። ይህም ስለምናገረው ነገር የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባህሪያትን በመምረጥ፡ ሁልጊዜ አብዝቼ በመጥቀሴ ነው። እንግዲህ፡ ያንን የማደርገው በምክንያት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ነገሮች የተጻፉት እኛ ልንመለከታቸው እንድንችል ነው። ብቸኛው ዘዴዬ ይህ ነው፡ ትምህርት ስለሌለኝ፡ ማድረግ የምችለው ብቸኛው ዘዴ፡ ወደ ኋላ ተመልክቼ እነዚህን በመጥቀስ ነው፡ "**ይህ** እንዴት ሆነ፡ በዛ ምክንያት ምን ተፈጠረ፡ **ይህ** የሆነው የት ነው በማለት ነው።" አያችሁ? እና እስኪ በዚያ ራሳችሁን አስቀምጡ።

97 በቅርብ ጊዜ፡ በመርከብ ላይ ስለነበረው ልጅ፡ ሰብኬ ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ ሸማግሌው ካፒቴን—ም ሞት አፋፍ ላይ ደርሶ ነበር። ታሞ ነበርና። እርሱም በመርከቡ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ካለ ጠየቀ። መጽሐፍ ቅዱስ የያዘውን ትንሽ ልጅ አገኙት፡ እርሱም መጥቶ ኢሳይያስ 53:5 አነበበ። "እርሱ ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፡ ስለ በደላችን ደቀቀ።" እና እንዲህ አለው፡ "ካፒቴን ሆይ፡ እናቴ ይህን እንዴት ስታነበው እንደነበረች፡ ል—ልንገርህ" አለው። እንዲህ በማለት፡ "አጻጻፏ እንዲህ ነበር፥ 'እርሱ ስለ ዊሊ ፕሩይት መተላለፍ ቆሰለ። ስለ ዊሊ ፕሩይት በደልም ደቀቀ። እነዚህ ሁሉ ነገሮችን ያደረገው፡ ለዊሊ ፕሩይት ነበር።'" ስሙ እንደዚያ ነበርና።

ሽማግሌው ካፒቴን፡ “ይህ ነገር ተመችቶኛል። ስሜን በዛ ውስጥ አስገብተህ ማንበብ ትችላለህን” አለው?

98 እርሱም፡ “እሰኪ ልሞክረው” አለ። እንዲህም አለ፡ “እሱ ግን ስለ ጆን ኳርትዝ መተላለፍ ቆሰለ። ስለ ጆን ክዋርትዝ በደል ደቀቀ። በመገረፉ ቍሰሉም ጆን ክዋርትዝ ተፈወሰ።”

ሰውየውም፡ “ገባኝ” አለ። ጌታም ፈወሰው። አያችሁ?

99 ስማችሁን እዛ ውስጥ አስገብታችሁ አንብቡት። ስለ ዊልያም ብራንሀም መተላለፍ ቆሰለ። ስለ ዊልያም ብራንሀም በደል ደቀቀ። ለእኔም ሆነ ለእናንተ ለሁላችንም፡ ይህን አድርጓል። ስማችሁ በዚያ ውስጥ አንብቡት።

100 እና፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ለህዝቤ ማምጣት የ—የምፈልገው በዚህ መንገድ ነው፡ እርሱን ለሚታዘዙት ሁሉ የሚያደርገው እንዲሁ ነውና። ለጥሪው ታማኝ ለሆነ ሰው ያደረገለት ነገር፡ እና ለጥሪው ታማኝ ላልሆነ ሰው ምን አደረገ፡ ከዚያ ስማችሁን በዚያው ውስጥ አንብቡት። በዚያ ቦታ ብትሆኑ ኖሮ፡ ምን ዓይነት አቋም ትይዙ ነበር? አስታውሱ፡ ዛሬ፡ ተመሳሳይ ዓይነት አቋም፡ የመያዝ መብት አላችሁ።

101 ኖኅ፡ እግዚአብሔር ስለተናገረው ቃል፡ ነቀፌታ ደረሰበት። ኖኅ፡ ተነቀፈ። ኖህ የኖረው ብዙ ሳይንሳዊ ሰኬቶች የመፈብረክ ችሎታ በነበረበት፡ በሳይንሳዊ ዘመን ነው፡ ያኔ ዛሬ እኛ ከሠራነው ከማንኛውም ነገር በላይ የላቀ ምርቶች ነበሩ። የተሻለ እውቀት፡ የተሻለ ክህሎት ነበራቸው። ሳይንሳቸው ከእኛ ይልቅ፡ እጅግ የላቀ ነበር። አስታውሱ፡ ለአንድ መቶ ሀያ ዓመታት በፌዘኞች ፊት፡ ስለ ሰበከው ቃል፡ ነቀፌታን መቋቋም ነበረበት። ታላላቅ ሳይንሳዊ ልቀቶቻቸው ሰማይ ላይ ዝናብ እንደሌለ አረጋግጦላቸው ነበር። ይሁን፡ እንጂ፡ ኖኅ የጌታን ቃል ሰማ፡ ይህም ከእነሱ አመለካከት ጋር ተቃራኒ ነበር። ስለዚህ፡ ሕይወቱ መዳን በፊት፡ እነዚህ ፌዘኞች ያቀረቡለትን ነቀፌታ በፊቱ ቆሞ መቋቋም ነበረበት።

102 ኦህ፡ ለምስኪኑ አዛውንት ሰባኪ ማዘናቸው፡ ምንም ጥርጥር የማይቀር ነው። በወቅቱ እንዲህ ዓይነቱ ቤት ብዙ ስላልነበረ፡ አላጋፋትም ወይም ሌላ ነገር አላደረጉትም። ጉዳት አልባ ነበርና። ማንንም ስለማይጎዳ፡ ዝም አሉት። “ቀጥል፡ ኮረብታ አጠገብ ውኃ በሌለበት ስፍራ፡ መርከብ የሚሰራ አክራሪው ሽማግሌ። ኦህ፡ እሺ፡ ምስኪን አዛውንት! ግን፡” እንዲህ አሉት፡ “ኖኅ ሆይ፡ ጀልባህን ለማንሳፈፍ፡ ውኃ ከየት ታገኛለህ? ”

“ከሰማይ ይወርዳል።”

103 “ከንቱ። እኛ ጨረቃ እና ከዋክብት፡ በራዳር መመልከት እንችላለን፡” ባላቸው ነገር ሁሉ መረመሩ። “ሰማይ ላይ ምንም ዝናብ የለም።”

ነገር ግን እሱ እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔር እዚያ ከላይ ያንን አደርጋለሁ ብሏል።”

“ይህን የሚያደርገው እንዴት ነው? ”

104 “ያ የእርሱ ጉዳይ ነው። እኔ ማድረግ ያለብኝ ብቸኛው ነገር ከዚህ እንድታመልጡ ማስጠንቀቅ ብቻ ነው።”

105 አሁንም ያው ነው። "እሳቱ ከየት ይመጣል?" ወንድሜ፡ ዛሬ ከኖህ ዘመን ይልቅ ትንሽ ግልጽ ነው። ከየት እንደሆነ አስቀድመን አይተናል። እርምጃውን ለመውሰድ ተዘጋጅቷል፡ በቃ። በ... በዚህ ጊዜ፡ ምንም ሰበብ የለም፡ ምክንያቱም ሳይንስ አስቀድሞ አግኝቶታል። አዎን፡ ወዳጄ።

106 ስለዚህ አሁን ያ በጣም ከባድ መሆኑን እናውቃለን። ስለዚህ ምስኪኑን ሽማግሌው ሰባኪ አዘኑለትና፡ እንዲቀጥል ተውት። አስተዋይ ነው ተብሎ የሚገመተው ሰው፡ የሰማይና የምድር ፈጣሪ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ አይነት ነገር ያደርጋል ብሎ ማመን፡ ወይም ሊያደርግ ያለውን ነገር፡ ይናገራል ብሎ ማሰቡ፡ ለእነርሱ ምናልባት፡ ለሰዎቹ እንግዳ ነገር ነበር፡ ከአስተሳሰባቸው ከነበራቸው ነገር ጋር፡ የሚጻረር ነበር። ምናልባት አልገባችሁም ይሆናል። ይኸውላችሁ። እ... እያንዳንዱን ተፈጥሮአዊ ነገር በሳይንስ ማረጋገጥ እንችላለን ብለው አሰበው ነበር። ታዲያ ይህ በዛሬው ጊዜ እንደምንኖርበት ዓለም በሳይንስ የተሞላ፡ ምሁራዊ ዓለም ዓይነት፡ አይደለም እንዴ! ሊያረጋግጡት የሚችሉት ማንኛውም ነገር፡ ስህተት ነበር፡ የእግዚአብሔር... "ምንም ነገር ይሁን እግዚአብሔር የተናገረው ነገር (እውነት ሆኖ ሳለ) በሳይንስ ተረጋግጦ ውሸት ሊሆን አይችልም።"

107 አሁን፡ ዛሬም ተመሳሳይ ሃሳብ አላቸው። ሐኪማችሁ ካንሰር እንዳለባችሁ፡ እንደሚትሞቱም ቢነግራችሁ፡ ሳይንስ ካንሰር እንዳለባችሁና፡ በከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ ቢያረጋግጥ፡ ከዚያ የተለየ ነገር ማሰብ የማይመስል ነው፡ ምክንያቱም ልትሞት ነው፡ በቃ። ሳይንስ ትሞታለህ ብሏል። መርምረውሃል፡ ይህም ተገኝቶብሃል። በቃ ትሞታለህ። እና እግዚአብሔር ይህን እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል ብላችሁ ለመናገር ብትሞክሩ እብደት ይመስላቸዋል። አያችሁ፡ ከዚህ በፊት እንደነበረው ሁሉ፡ ነቀፌታውን መቋቋም አለባችሁ።

108 እንዲህ ይላሉ፡ ዶክተሩ እንዲህ ብሎሃል፡ "እኛ ዘልቀን መርምረናል፡ ካንሰሩ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ነው። ኦፕራሲዮን አድርገንሃል። በሰውነትህ በሙሉ፡ በልብህ፡ በሳንባህ፡ በጉበትህ፡ በሁሉም ቦታ ተሰራጭቷል። የማይቻል ነገር ነው።"

ስለዚህ፡ አያችሁ፡ እናንተም "ያም ሆነ ይህ፡ በሕይወት ይኖራል፡" ትላላችሁ።

እነሱም "መቼም፡ ምስኪን ሰው ነው፡ ናቁት በቃ፡" ይላሉ።

109 ትዝ ይለኛል አንድ ምሽት። ቢል ሆል፡ የሚልታውን ቤተክርስቲያን ወንድም ሆል፡ ብዙዎቻችሁ ጉዳዩን ታስታውሱታላችሁ። ወደዚያ እንድሄድ... ጠሩኝ። ሚስቴ፡ የሚስቴ-እናት-እማቼ እና እኔ ሆነን፡ ወደዚያ አመራን። ይመስለኛል፡ የከተማው ከንቲባ፡ ወይም እዚህ ዳኛ የነበረ፡ የጆርጅ ኩፕ እኅት፡ ያገባ ይመስለኛል። የሚስቴ-ወንድም-አማቼ... ነበረ። መሞቱ ስለማይቀር ወደዚህ አመጡት። በሚልታውን የሚገኘው ሐኪም፡ ኒው አልባኒ የሚገኘው ሐኪም፡ ጉዳዩ የጉበት ካንሰር እንደሆነ አረጋግጦ ነበር። ስለዚህ ወይዘሮ ሆል ለማየት ወረድኩ። ጃንዳይስ ጀማምሮት ነበረና፡ ሰውነቱ በሚሉ ወደ ቢጫነት ተቀይሮ ነበር። እኔም "በቃ፡ ይሄ ሰውዬ የሚሞት ይመስለኛል፡" አልኳት። አልኳትም...

110 እርሷም፡ "ወንድም ቢል፡ በሆነ መንገድ ከ... ከእግዚአብሔር መስማት የምትችልበት ነገር አለን" ብላ ጠየቀችኝ?

እኔም፡ “አ—አላውቅም፡ እህት ሆል። መጸለይ እችላለሁ” አልኳት።

111 ጸለይኩ። ወደ ቤት ተመለስኩና፡ ጌታ ምንም አልነገረኝም። ከዚያም በቀጣዩ ቀን፡ ተመልሼ ሄጄ፡ እንደገና ጸለይኩ።

እርሷም፡ “ጥሩ ሐኪም ታውቃለህ” ብላ ጠየቀችኝ?

112 እኔም፡ “እንግዲህ፡ የቤተሰባችን ሐኪም ጀፈርሰንቪል ውስጥ የሚኖር አለ፡ ዶክተር ሳም አዴር ይባላል” አልኳት። አ—አ—አ... አባቱ የቤተሰባችን ሐኪም ነበር። ወጣቱ ሳምና እኔ ሁሌም የቅርብ ጓደኞች ነበርን፡ በ—በተመሳሳይ ጊዜ ወደ ትምህርት ገባን፡ አብረን ነው ያደግነው። ችግር ሲያጋጥመን ሁሌም ወደ እሱ እንሄዳለን” አልኳት።

እርሷም እንዲህ አለች፡ “ቢል ሆልን ለማየት ሊመጣ ይችላልን? ” ቢል ሆል ባለበቷ ነው።

እኔም “እጠይቀዋለሁ፡” አልኳት።

113 ሳምም እንዲህ አለኝ፡ እንግዲህ፡ አለ፡ “ቢሊ፡ ሐኪሙ ካንሰር እንዳለበት ከተናገረ፡” እንዲህ አለ፡ “እኔ ማድረግ የምችለው፡ አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ከእኔ የበለጠ ብልህ ወደሆነ ሰው፡ ወደ ስፔሻሊስት እልከዋለው። የኤክስ-ሬይ እናነሳዋለን፡ ከእንግዲህ ችግር ውስጥ አናስገባውም” አለ።

114 ወደ ኒው አልባኒ ላክንና እዚያ ካለው ዶክተር የኤክስ-ሬይ ውጤቶችን አመጣን። ወደ ሉዊስቪል ወሰደው መረመሩት፡ በአምቡላንስ ወሰደው፡ መልሰው አመጡት።

115 እና፡ እርግጥ ነው፡ ችግሩ ለወይዘሮ ሆል መናገር አይችልም ነበርና፡ ስለዚህ እኔን ጠራኝ። እንዲህ አለኝ፡ “ሰባኪው ጉደኛህ፡” “ይሞታል፡” አለኝ። እንዲህ አለኝ፡ “በሉዊስቪል የሚገኘው ስፔሻሊስት አሁን ደውሎልኛል፡ እናም እንዲህ አለኝ፡ ‘በሚልታውን የሚገኙት ዶክተሮች፡ የ—የ... የሰጡት ምርመራና፥ በኒው አልባኒ የሚገኘው ዶክተር የሰጠው ምርመራ፥ ትክክለኛውን ዓይነት ምርመራ ነው።’” አለኝም፡ “ይህ የጉበት ካንሰር ነውና፡ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። እና፡ ቢሊ፡ የሰውየውን ጉበት አስወጥተን፡ እሱን በሕይወት ማስቀጠል አንችልም።” “ይሞታል። ሰባኪ ከሆነ ደግሞ፡ መዘጋጀት አለበት፡” አለኝ።

116 እኔም እንዲህ አልኩት፡ “ጥያቄው ይህ አይደለም። ዕድሜው ግን ከሃምሳ-አምስት ዓመት አይበልጥም፡ ለመሰበክ፡ ስለዚህ ገና ብዙ ሕይወት አለው።” እና “እሺ፡ የሚሞት ከሆነም፡ ነገሩን መቀበል ነው። አመሰግናለሁ፡ ዶክተር ሳም፡” አልኩት።

117 እኔም ወረድኩና ወይዘሮ ሆልን ጠራኋትና፡ ነገርኳት። እኔም፡ “ወይዘሮ ሆል፡ ሳም የሉዊስቪል ምርመራ በኒው አልባኒ እና ሚልታውን ውስጥ እንደነበረው ተመሳሳይ ነው ብሏል። ሰውዬው እየሞተ ነው። ወንድም ሆል ሊሞት ነው። የጉበት ካንሰር ይዞታል፡ እና በከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል” አልኳት።

118 እሷም ማልቀስ ጀመረች። ዞር ብዬ፡ አብሬው ጸለይኩ። እና ያን ጊዜ፡ እኔ ክፍል ውስጥ መሆኔን እስከማያውቅ ድረስ፡ ከአቅሙ በላይ ሆኖበት ነበር።

119 ስለዚህ፡ ተመልሼ መጣሁ። በዚያን ጊዜ፡ ብዙ ሰዎች ወደ ቤታችን ይመጡ ነበር። መስክ የወጣ አንድም ሰው አልነበረም። ተላላፊ አልነበረውምና፡ ሰዎች ከየትኛውም ቦታ ይመጡ ነበር።

120 ትንሽ ዕረፍት ማድረግ ፈልጌ ነበር። ስለዚህ ወደ ውስጥ ገባሁ፡ በጥዋት፡ ወደ ሁለት ሰዓት-ተኩል፡ ወይም ሦስት ሰዓት ገደማ ተነሣሁ። ወንድም ዉድ ገና ከቦታው አልተንቀሳቀሰም ነበር። ወደ ሜዳው ላይ ተመለከትኩ፡ እዚያም፡ ማንም አልነበረም፡ ስለዚህ የድሮውን ባርኔጣዬን አደረኩና ወደ እንግዳ ክፍል ገብቼ፡ ባለ 22 ጠመንጃዬን አነሳሁ። ወደ ሰምንት ሰዓት እስኪደርስ ድረስ ወጥቼ፡ ሽኮኮ ለማደን ሄድኩ። ከዚያም አንድ ዛፍ አጠገብ ቦታ አግኝቼ ትንሽ እንቅልፍ ተኛሁ። በቤት ውስጥ ልታገኙት አትችሉም።

121 ባርነጣዬን አጥልቄ ክፍሉ ውስጥ እመላለስ ነበር። ግድግዳው ላይ የተንጠለጠለ አፕል አየሁ። በ—በጣም የተበላሸ አፕል ነበር። በትል-የተበላ፡ የበሰበሰ፡ በሁሉም ቦታ የቆሸሸ ነበር። እኔም፡ “ሜዳ ይህን ግድግዳው ላይ ለምን ሰቀለችው” ብዬ አሰብኩ?

122 ከዚያም በድጋሜ፡ አስተዋልኩና፡ ግድግዳው ላይ አልነበረም። በአየር ላይ ተንጠልጥሎ ነበር። አሮጌውን ባርኔጣዬን አውልቄ፡ ጠመንጃውን ጥግ ላይ አስቀመጥኩና፡ በጉልበቴ ተደፋሁ። እኔም አልኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ አገልጋይህ ምን እንዲያውቅ ትፈልጋለህ? ”

123 ሌላም መጣ፡ ሌላም ደግሞ መጣ፡ እስከ አራት ወይም አምስት የሚደርስ አፕል (በየትኛው እንደነበረ አሁን ረስቻለሁ) በዚያ ተንጠልጥለው ነበር። ከዚያም በጣም ትልቅ፡ ቄንጆ አፕል፡ ሽንጉርጉር የሆነ አፕል፥ በጣም ትልቅ፡ ጤናማ-የሚመስል አፕል፡ ወደ ታች ወረደና ሌሎች የተበላሹ-የሚመስሉ አፕሎችን ይበላቸው ነበር። እና እሱም፡ “ተነስ። በእግርህም ቁም” አለኝ። እንዲህ አለኝ፡ “ሂድ፡ ቢል ሆልን፡ አትሞትም ብለህ ንገረው። በሕይወት ይኖራልና” አለኝ።

124 ኦህ፡ የቻልኩትን ያህል በፍጥነት ሮጥኩ፡ እና እንዲህ አልኩ፡ “ወይዘሮ ሆል፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**። አይሞትም በሕይወት ይኖራል።” እሱም ሰማኝ። እርሱም ለማልቀስ ሞከረ፡ ከዚያ በላይ ግን የመናገር አቅም አልነበረውም።

125 ተመልሼ ሳምን ጠራሁት። እና፡ “ሳም፡ ወ—ወንድማችን በሕይወት ይኖራል” አልኩት።

እርሱም፡ “እንደዚህ እንዴት ሊኖር ይችላል” አለኝ?

126 እኔም “እንዴት እንደሆነ እኔ አላውቅም። እግዚአብሔር ተናግሯል። ስለዚህ ይሆናል፡” አልኩት።

127 ዛሬም በህይወት አለ። ይህ ከአሥር ዓመት ገደማ በፊት ነበር። ጠንካራና ጤናማ ሰው ነው። ሚስቱ ከዚያ በኋላ ሞተች። ዳግመኛ አግብቷል።

128 በጆርጅ ራይት፡ እና ሌሎች ልንዘረዝራቸው የምንችላቸው ብዙዎች፡ የሚሆነው እንዴት ነው? ይህ ምንድን ነው? ይህም ነቀፌታውን ለመቋቋም ነው። ይሳለቃሉ እንዲሁም ያሾፋሉና።

129 የ 1937ቱ ጐርፍ ከመከሰቱ በፊት አስታውሳለሁ። እኔ ከፎልስ ሲቲ ትራንስፈር ኩባንያ ጋር ነበርኩ፡ ስለነዚህ ነገሮች እየነገርኳቸው ነበር፡ ሠላሳ-ሁለት ጫማ የሚያክል ውኃ በስፕሪንግ ጐዳና ላይ፡ እንደሚመጣ እየነገርኳቸው ነበር፡ እዚያ እንደሆነ አምናለሁ። ሁሉም ሳቁብኝ። እንዲህ አሉ፡ "ምስኪን ቢሊ። ይህ ልጅ... ምን ነካው!" በዚያን ጊዜ ገና ልጅ ነበርኩና። እንዲህ አለ፡ "ቢሊ ጥሩ ልጅ ነው። በሁሉም ነገር ግራ መጋባቱ ያሳዝናል" አለ። እኔ ግን ግራ አልተጋባሁም። ወደ **ውስጥ** ተጠምቄ ነበር እንጂ፡ ግራ አልተጋባሁም። ወደ "ውስጥ" ብቻ። እንደዛ ልክ እንደተናገርኩት ሆነ።

130 እየተናገርኩ እያለሁ፡ እኅት ሐቲ ራይትን አስተዋልኳት፡ ይመስለኛል፡ እዚያ ተቀምጣለች። ስለ ቢል ሆል ጉዳይን ታስታውሳለች። ሰንቶች። ዛሬ ጠዋት እዚህ ከተገኛችሁ፡ ጉዳዩን የምታስታውሱት፡ ሰንቶቻችሁ ናችሁ? ኦህ፡ ማይ! እርግጥ ነው። ብዙዎቻችሁ ነበራችሁ።

131 አሁን፡ ለእኛ ያዝናሉ፡ በፌዘኞች ዘመን፡ ቃሉን ለማክበር ለሚሞክር ሰው ሁሉ ያዝናሉ። ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ ነቀፌታ መምጣቱ አይቀርም። ሁሌም እንዲሁ ነበር። በወቅቱ እንዳሰቡት ሁሉ፡ ሁሉም ነገር፡ በሳይንስ ከተረጋገጠ በኋላ፡ እግዚአብሔር፡ ሳይንስን የሚፃረር ነገር አይናገርም ብለው ያስባሉ። እንግዲህ፡ አምላክ እንዲሆን ያደረገው ይህ ነው። የሱ ነገሮች ሳይንሳዊ መሠረት ያደረገ ቢሆን ኖሮ፡ ሰው ሊደርስበት ከሚችለው በላይ አይሆንም ነበር። ነገር ግን፡ እርሱ እግዚአብሔር ነው። እ—እርሱ የሳይንስ ፈጣሪ ነው። የፈለገውን ማድረግ ይችላል።

132 እንዲህ ሳያስቡ አይቀሩም፡ "ኖኅ ምስኪኑ ሽማግሌ፡ በቃ፡ ተዉት ያን ሽማግሌ። በዚህ ዘመን ያገኘነው ደስታ ሁሉ ያጣ ሰው ነው፡ ስለዚህ ተውት።" አሁንም ተመሳሳይ ነገር እየሆነ ነው።

133 አሁን፡ ግን፡ እዚህ ላይ ሌላ ነገር መናገር እፈልጋለሁ። አሁን፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን እምነቱን እናድንቅ። በኖኅ ዘመን ኖረን ቢሆን ኖሮ፡ ኖህ የወሰደውን አይነት ተመሳሳይ አቋም፡ እንወሰድ ነበር ይሆን ብዬ አስባለሁ? እውነትን ተከትሎ የሚመጣውን ነቀፌታ ለመቋቋም ፈቃደኞች እንሆናለንን? በወቅቱ በዓለም ላይ ከነበሩት በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች መካከል፡ ለዚህ እውነት የቆሙት ኖኅና ቤተሰቡ ብቻ ነበሩ። አስባችሁት ታውቃላችሁ? ይህ ሰውና ሦስቱ ልጆቹ፡ የልጆቹ-ሚስቶች-አማቾቹ፡ እና ሚስቱ፡ ብቻ ናቸው ለእውነት የቆሙት። ይሁን እንጂ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ይዘው ነበር። ወደኋላ መለስ ብለን ሰናስበው እናደንቀዋለን። እስኪ እንደገና እናስበው?

አሁን በልጆቹ ስጦታዎች ምክንያት መፍጠን አለብኝ።

134 አብርሃም፡ **አብርሃም** የሚለው ቃል ራሱ "የብዙዎች አባት" ማለት ሲሆን፡ ይህም "የትውልዶች አባት" ያደርገዋል።

135 አሁን፡ አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቷል። አብርሃም ነቢይ ነበር፡ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቷል። አብርሃምንም የእግዚአብሔርን ቃል በመያዙ እናደንቀዋለን፡ እንዴት ከዘመዶቹ እንደተለየ፡ ለአብርሃም ምን ያህል ከባድ እንደነበረ። ያደገው እዚያ ነው። ከባቢሎን ወርዶ፡ በ—በሺናርና በከለዳውያን ምድር፡ በ—በ—በኡር ከተማ በነበረበት ጊዜ፡ አጋሮቹ፡ ሕዝቡና፡ አብረውት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱትና፡ ሁሉ ነገር ነበሩት። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር፡

“ራስህን ለይ” አለው። ኦህ፡ ማይ! በጣም የሚወደውንና፡ ለእሱ እውነተኛ የነበረውን ነገር ሁሉ፡ ትቶ መሄድ፡ ምንኛ አስከፊ ነገር ነበር። እግዚአብሔርም፡ “ራስህን ለይ” አለው።

136 በጣም እንግዳ ነገር ተናገረው። “ከሚስትህ ልጅ ትወልዳለህ” አለው። የሰባ-አምስት ዓመት ነበር፡ እርሷም ሰድሳ-አምስት ነበረች። እንደ ሴቶች ወግ፡ ልጅ የሚወልዱበት የመውለጃ የሴት ወግ ከራቃት፡ አመታት አስቆጥራለች። እዚህ ጋር፡ ከልጅነቷ ጀምሮ ከሷ ጋር ከኖረ በኋላ፡ ግማሽ እህቱ ስለነበረች፡ ከሷም እንዴት ያንን ልጅ ሊያመጣ ይችላል? አብርሃምም በባልደረቦቹ መካከል ወጥቶ፡ እንዲህ ሲል አሰቡት፡ “ሳራ እና እኔ፡ ልጅ እንወልዳለን።” እንዲህ ሲል ማሰብ ትችላላችሁ? ይህን መገመት ትችላላችሁን?

137 ለምን፡ ሕዝቡም፡ “ይህ ምስኪን አዛውንት፡ የሆነ ችግር አለበት” ይሉታል።

138 ነቀፌታ ነው፡ ነገር ግን አብርሃም ያንን ነገር አጥብቆ ያዘ። መቶ ዓመት ሲሞላው፡ በእግዚአብሔር ቃል በጭራሽ አላመነታም። አሁንም ነቀፌታውን ተቋቋመ፡ እርግጥ ነው፡ አጥብቆ ይዟል።

139 ልዩነቱን አስተውላችኋል? ሣራ አብርሃምን፡ ማለቴ፡ እግዚአብሔርን፡ በራሷ፡ ትንሽ ለማገዝ ሞከረች። ያሰበችው፡ ታውቃላችሁ፡ እግዚአብሔር ቃል ከገባው፡ በተቃራኒ ነበር። “አሁን፡ እኔ አሮጊት ሴት እንደሆንኩ፡ ታውቃለህ፡ ነገር ግን አጋር ቈንጆ ሴት ናት። አብርሃምም እሷን ቢያገባ፡ አይከፋውም። ስለዚህ፡ ታውቃላችሁ፡ ያ—ያም እግዚአብሔርን ያግዘዋል። ያ እግዚአብሔርን ያግዘዋል፡ ምክንያቱም አጋር፡ እዚህ፡ ምናልባት ሀያ ዓመቷ ናት። አገልጋዬም ናት። ምን እንደማደርግ ታውቃላችሁ? ለባለቤቴ፡ እንደ ሚስት እሰጣታለሁ፡” ምክንያቱም ብዙ ሚስት ማግባት ሕጋዊ ነበር። ስለዚህ እንዲህ አለች፡ “እሰጠዋለሁ፡ እሷም ከባለቤቴ ልጅ ትወልዳለች፡ ከዚያም እኔ ልጁን እወስዳለሁ። እግዚአብሔር ቃል የገባውም፡ ይህ ነው” አለች።

140 አያችሁ፡ ሁሌም አንድ ነገር ለማድረግ እንሞክራለን፣ እርሱን መጠበቅ አንችል። ራሳችን፡ የሆነ ነገር ማድረግ እንፈልጋለን። ሁሉም ነገር መልካም ሊሆን ይችላል። ቈንጆ ልትሆን ትችላለች። ይህ በጣም ጥሩ ሊመስል ይችላል፡ ነገር ግን በቃሉ መሠረት አልነበረም። እግዚአብሔር ለአብርሃም ሣራ ልጅ እንደምትወልድ ነግሮት ነበርና።

141 ስለ ታናሹ መንጋ የተናገረውን ታስታውሳላችሁን? “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።” “በኖኅ ዘመን እንደነበረው ሁሉ፡ የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል፡ በዚያ ጊዜ ጥቂቶች፡ ማለትም ሰምንት ነፍሳት፡ ብቻ ዳኑ።” እነዚያ ቃላት ሊሻሩ አይችሉም፡ ስለዚህ እራሳችንን እንንቃና ከቃሉ ጋር እንጽና። በጣም ጥሩ። አያችሁ?

142 ሰዎች ሁል ጊዜ አንድ ነገር ለመፈብረክ ይሞክራሉ፡ የእግዚአብሔርን የፈጠራው ፈቃድ ቦታ ለመያዝ ይሞክራሉ። አያችሁ፡ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ እንደነገርኳችሁ፡ ምናልባትም በቤተ ክርስቲያን ፊት፡ በ፡ ታውቃላችሁ፡ “ጥቂት ሱፍ ትሠራልኛለህ? ” ብላችሁ በግን መጠየቅ አትችሉም፡ በጭራሽ፡ ማንም አይችልም። አሁን፡ ፍየል ሱፍ ማምረት አይችልም፡ ምክንያቱም ተፈጥሮው አይፈቅድለትም። ምንም ያህል የበግ ሱፍ ፍየል ላይ ለማሰር ብትሞክሩም፡ አይሳካላችሁም። ፍየል ሱፍ መፈብረክ አይችልም፡ በግ ደግሞ ጸጉር መፈብረክ

አይችልም። በግ ስለሆነ ግን ሱፍ ያወጣል። እሱ የሚያደርገው ይህ ነው። አይፈበርክም።

143 የመንፈስ ፍሬዎችን መፈብረክ አያስፈልግም። የመንፈስን ፍሬ ማፍራት አለብን እንጂ። የአፕል ዛፍ አፕል አይፈበርክም፡ ያፈራዋል ምክንያቱም የአፕል ዛፍ ስለሆነ።

144 ማንኛውንም ነገር ለማምረት ከሞከርን፡ "ጉዳዩን እኔ ራሴ እገዘዋለው። በሴሚናሪው ውስጥ ለአስር ዓመት እማራለሁ። **ይህንን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን** እማራለሁና፡ የሥነ ጥበብ የመጀመሪያ ዲግሪዬን እና የዶክትሬት ዲግሪዬን እወስዳለሁ። ለብቻዬ፡ ጌታን እገዘዋለው።" ይህ አይሠራም።

145 እግዚአብሔር፡ አስቀድሞ በመወሰን፡ የፈለገውን ይጠራል። መንግሥቱን ሊሰጥ ለሚፈልገው ሁሉ ይሰጣል። ያንን ከናቡከደነፆር ተምረናል።

146 ያንን በ—በኤርምያስ ላይ ተምረነዋል፡ እግዚአብሔር ለኤርምያስ፡ በጌታ ቃል በነገረው ጊዜ፡ እስራኤላውያን ለሰባ ዓመታት በባቢሎን በግዞት የሚኖሩበት ጊዜ እንደሚመጣ፡ ነገረው። እናሆ ሌላ ነቢይ መጣ። እርሱ አስቀድሞ ነግሮታል፡ እንዲህ አለው፡ "አሁን፡ እናንተ ነቢይ ይኖራችኋል፡ ይነሣል። በዚያ በባቢሎን ማዶ፡ ሕልም አላሚዎችና ነቢያት፡ ይነሳሉ፡ ከዚህ ጋር የሚቃረኑ ትንቢቶችን ይናገራሉ። ነገር ግን ሕዝቡ እነዚህን ሰዎች እንዳያዳምጧቸው ንገራቸው።"

147 ከ—ከነቢያት አንዱ የሆነው፡ ሐናንያ፡ የተባለ ሰውም መጣ። ኤርምያስም በዚያ እንገቱ ላይ ቀንበር ይዞ ቆሞ ሳለ፡ ሐናንያ መጥቶ፡ እንዲህ አለ፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ፡ የጌታን ዕቃ ሁሉ... " አሁን፡ በመሠረቱ፡ በጣም ጥሩ ይመስላል። "እግዚአብሔር ሕዝቡን ይባርካል። በሁለት ዓመት ውስጥ፡ ሁሉንም ነገር ወደነበረበት ይመልሳል።"

148 መጽሐፍ ቅዱስም ሲናገር፡ ነቢዩ ኤርምያስ እንኳ፡ "አሜን። አሜን። ሐናንያ ሆይ፡ ጌታ ቃልህን እንዲፈጸም ያድርግ። ይሁን እንጂ ሐናንያ፡ እስቲ አንድ ነገር እናስብ። ከኛ በፊት የነበሩ ነቢያት፡ ስለ ታላላቅ መንግሥታት፡ ስለ ጦርነትና የመሳሰሉት ትንቢቶች ተናግረዋል። ይሁን እንጂ፡ ነቢዩ የሚታወቀው ትንቢቱ ከተፈጸመ በኋላ መሆኑን፡ ማስታወስ ይኖርብናል" አለ። አያችሁ?

149 ከዚያም ሐናንያ መጥቶ፡ ከኤርምያስ አንገት ላይ ያለውን ቀንበር፡ በካህናቱና በጉባኤው፡ ምናልባትም በአንድ ሚሊዮን ተኩል ሰዎች ፊት ወሰደው። እግዚአብሔር በኤርምያስ አንገት ላይ፡ ለምልክነትን የጫነውን ቀንበር፡ ወስዶ ሰበረውና፡ መሬት ላይ ወርውሮት፡ በማጓጓት፡ እንዲህ አለ፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ፡ ተመልሰው ይመጣሉ" አለ።

150 ኤርምያስ ወደ እሱ ተመለከተ። ይህ ከቃሉ ጋር የሚቃረን ነበረ፡ ወዲያውኑም ሄደ። እግዚአብሔርም፡ "ወደ ኋላ ተመልሰህ ንገረውም" አለው፡ እሱም፡ "እኔ እሱን በፍጹም አልተናገርሁትም" አለው።

151 በጣም ተነቃቅቶ ነበርና። የራሱን ስሜት ተከተለ። አያችሁ? የሚናገረው እግዚአብሔር አለመሆኑን፡ እስኪያየው ድረስ ወይም እስከሚያውቅ ድረስ

አልጠበቀም። በጣም ተነቃቅቶ፡ ወደ ኋላ ተመለሰ። እ...

152 ዛሬ በመላ አገሪቱ፡ ተመሳሳይ ነገር፡ እናገኘዋለን። በቅርብ ጊዜ አንድ ቴፓችን በአንድ ቤት ውስጥ እየተደመጠ ነበር፡ በዚያም የተወሰኑ የአገልጋዮች ሕብረት እምነታቸውን ስላረጋገጡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመጠመቅ መጡ። አንድ ሰውም ከክፍሉ ተነሥቶ፡ በልሳኖች እየተናገረ እንዲህ አለ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**። ያላችሁን ጠብቁ። እንዲህ ማድረጋችሁን፡ ቀጥሉ፡ እኔም እባርካችኋለሁ” አለ።

153 እነሱም፡ “ደህና፡ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ከተናገረ፡ በቃ ያ ነው ማለት ነው” አሉ። አያችሁ፡ በቃሉ አልተመረመረም። በመጀመሪያ ቃሉን፡ መቀበል አለበት። ይሄውላችሁ። ከቃሉ ጋር ተቃራኒ ሆነ።

154 ኤርምያስ ተመልሶ መጣ፡ የተቀባው ነቢይ። እግዚአብሔርም ነገረው፡ እንዲህ አለው፡ “ሐናንያ እኔ በአንገትህ ላይ ያስቀመጥኩትን፡ የእንጨት ቀንበር እንደሰበረ አውቃለሁ፡ እኔ ግን የብረት ቀንበር እሠራልሃለሁ።” እንዲህም አለ፡ “ባሪያዬን፡ ናቡከደነፆርን ያገለግሉት ዘንድ የወረዱት እነዚህ አሕዛብ ሁሉ፡” እርሱም አረማዊ ነበር። አያችሁ? እስራኤልም፡ መሥዋዕታቸውን ሁሉ ያቀርቡ ነበር፡ እነሱ ግን... አያችሁ?

155 እግዚአብሔር፡ እባርካለሁ ብሎ ቃል ገብቷል፡ ነገር ግን በረከቶቹ በመስፈርቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ያ በረከት እንዲሰራ ከፈለጋችሁ፡ መስፈርቶቹን ማሟላት አለባችሁ።

156 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ እዚህ ከትንሽ፡ መልከ መልካም ልጃገረድ ጋር፡ ቁጭ ብዬ ነበር። በመጀመሪያ፡ በዚያ ቤተሰብ ውስጥ፡ ስሕተት የሆነ ነገር ካለ፡ አጣራሁ። እግዚአብሔር ይፈውሳል፡ ነገር ግን ቅድመ ሁነታዎች አሉ። አያችሁ? ያገኘሁት፡ ብቸኛው ነገር፡ እናትየዋ መድኃኒት መውሰድ ስሕተት ነው የሚል ስጋት ነበራት። እንዲህ አልኳት፡ “እንደዛ አታስቢ፡ እህቴ። ያንን ከአእምሮሽ አውጪ። ልጅሽን ይዘሽ ሂጂ። መድኃኒቱን ስጫት። እግዚአብሔር ይህን ያሳውቀናል።” አያችሁ?

157 አሁን፡ ግን፡ ነገሩን፡ ፈልጉ፡ እወቁ። ከዚያም፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ከሆነ፡ እሺ።

158 አሁን እዚህ ላይ እንደምናገኘው፡ እነዚህ ሰዎች፡ አንድ ነገር ለመፈብረክ እየሞከሩ ነበር፥ አጋር—እና ሣራ፡ አብርሃምን ለመርዳት፡ እግዚአብሔር የገባው ቃል እንዲፈጽም ለመርዳት የሆነ ነገር አደረጉ። ያንን ማድረግ አትችሉም። ይህን ማድረግ የሚቻልበት፡ ምንም፡ መንገድ የለም። ይህ ከ—ከሁሉም ነገር ጋር የሚቃረን ነው። ያም ሆነ ይህ፡ የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸማል። በቃሉ ላይ በትክክል መቆም አለባችሁ፡ “**በዚህ** መንገድ ነው፡” በሉና፡ ቃሉን ጠብቁ። አሁን፡ ተመልከቱ፡ ቃሉን የሚተካ ነገር ለማዘጋጀት ፈለጉ!

159 ምናልባት የአብርሃም፡ ወዳጆችም ቢሆኑ፡ አስተውለን ከሆነ፡ ምናልባት የአብርሃም ጓደኞች ይመጡና እንዲህ ይላሉ፡ “እሺ፡ የአህዛብ አባት፡ አሁን ስንት ልጆች አሉህ? መቶ አመት ሞልቶታልና። “እንዲህ ይላሉ፡ የአህዛብ አባት፡ የብዙዎች አባት ሆይ፡ አሁን ስንት ልጆች አሉህ? ” ፌዘኞች!

160 አሁንስ፡ ጊዜው አይታይህምን? አንዳንድ ጊዜ የምንጸልየው ነገር፡ ሳይፈጸም ሲቀር፡ አይተን እናውቅምን?

161 “ይህ እዚያ ጋር የሚቀመጠው አዛውንት፡” ይሉታል። “ዕውር ነው። ደንቆሮ ነው። ዲዳ ነው። በሽተኛ ነው። **ይሄንን** አድርጓል። አንተ መለኮታዊ ፈዋሽ፡ እስኪ ሂድና ፈውሰው። ያን ጊዜ እናምናለን።”

162 ያንኑ ዲያብሎስ እንዲህ ብሎ የተናገረው እርሱ እንደሆነ አስተውለው ይሆን፡ “ከመስቀሉ ውረድና፡ አምንሃለሁ። እነዚህን ድንጋዮች ወደ ዳቦ ቀይርና፡ ያን ጊዜ አምንሃለው”? አያችሁ? በጌታችን አይኖች ላይ ጨርቅ አስሮ፡ ራሱን በበትር የመታው ያው ዲያብሎስ እሱ ራሱ ነው፡ እንዲህም አለው፡ “አሁን፡ አንተ ነቢይ ከሆንክ፡ ማን እንደመታህ ንገረን፡ እናምንሃለን።”

163 ይኸውላችሁ፡ ማን እንደመታው ያውቃል። እነዚያን ድንጋዮችም ወደ ዳቦ ሊለውጣቸው ይችል ነበር። ከመስቀል ሊወርድም፡ ይችል ነበር። ነገር ግን ቢወርድ ኖሮ እኛ ዛሬ ምን እንሆን ነበር? አያችሁ? የእግዚአብሔርን ፕሮግራም አላወቁትም። እግዚአብሔር ቃል የገባውን ነገር ማወቅ አለባችሁ።

አሁን ቶሎ እንፍጠን።

164 አሁን፡ አሁን እንዲህ ብለውት ይሆናል፡ “የአህዛብ አባት ሆይ፡ ከሀያ-አምስት ዓመታት፡ በፊት ጀምሮ፡ ከሣራ ልጅ እወልዳለሁ፡ ከዚያም የህዝብ ወገኖች ይወጣሉ ብለህ ስትናገር ሰምተናል። የአሕዛብ አባት ሆይ፡ አሁን በዚህ ወቅት ስንት ልጆች አሉህ? ” ኸሃ! አያችሁ? ያ ትችት የሚተቸው ያረጀ የትችት መንፈስ ነው።

165 አብርሃም ምን አደረገ? እንዲህ አለ፡ “በአለማመን፡ በተሰፋው ቃል ላይ አላመንታም።”

“ለምን፡ **ለእከሌ-እና-ለእከሊት** ሰው ጸልየህ ነበር፡ እነሱ ግን አልተፈወሱም።”

166 ይህ ለውጥ አያመጣም። ዛሬ ሌሊት ለአሥር ሺህ ብጸልይና፡ አሥር ሺህም በጠዋት ላይ ቢሞቱ፡ ነገ ማታ አሁንም ድውያንን ዘይት እየቀባሁ እየጸለይላቿለሁ። እግዚአብሔር ብሏልና። ያ ትንሽ እንኳን፡ አያስቆመውም። እግዚአብሔር ቃል ገብቷል። አምነዋለሁ። በእርግጥኛነት። አሁንም፡ የሚናገሩት ነገር ምንም ለውጥ አያመጣም። ነገር ግን፡ ያፌዙባችኋል። ይህ የቃሉ ነቀፌታ ነው።

167 አብርሃም፡ ለእግዚአብሔር ቃል ቆሞ፡ በመጨረሻ ተፈጸመ። ኦህ፡ ማይ!

168 መሃንነት የሚያስከትለውን መሳለቂ-ያ ተመልከቱ። መሳለቂያ መሆን፡ በመጀመሪያ፡ መሃንነት የሚያስከትለውን ነቀፌታያ ነው። ለ... ለእነዚያ ሁሉ ዓመታት መካን ናት የሚል ነቀፌታ መቋቋም ነበረባት። ዕድሜዋ ወደ አንድ መቶ ዓመት ገደማ ነበር። እርሷም **ልዕልት** እንደምትሆንና፡ የዚህ ልጅ እናት እንደምትሆን የተነገረላት፡ የእግዚአብሔር ቃል በዘጠና ዓመቷ ላይ ነበር። እርስዋም አብራሃምም፡ መካን ሆነው፡ ሰ—ሰውነታቸውም ሞቷል፡ ነገር ግን ቃሉን ትንሽም ብሆን፡ ፈጽሞ አልተጠራጠሩም። ነገር ግን በመጀመሪያ፡ ያንን መቋቋም ነበረባቸው። ከዚያም፡ ሃሌሉያ፡ እግዚአብሔር ቃሉን ጠብቋል፡ በዚያ ጨለማ ሰዓት፡ ይስሐቅ ተወለደ። “ዘሮቹም እንደ ባሕር አሸዋ ወይም

እንደ ሰማይ ከዋክብት ናቸው።” አያችሁ? እግዚአብሔር ምንጊዜም ቃሉን ይመልሳል። አዎን። በመጀመሪያ መሃንነት፡ ከዚያም ይሰሐቅ።

169 ዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ፡ በተመሳሳይ፡ ያ አዛውንት እና አዛውንቷ ሴት፡ አሁንም ቃሉን በመያዝ ቀጠሉ። ዘካርያስ ወደዚያ ወጣና፡ ብራናው ላይ ጻፈ፡ እንዲህም አለ፡ “አንድ መልአክ ተገናኘኝ፡ ከኤልሳቤጥ፡ እዚህ ከአሮግቷ ባለቤቴ ጋር ልጅ እንደምወልድ ነገረኝ። ከእንግዲህ መናገር አልችልም። እኔ ዲዳ ነኝ። እስከሚወለድበት ቀን ድረስ ዲዳ እሆናለሁ። ሆኖም የሚመጣው፡ ሕፃን የልዑሉ አምላክ ነቢይ ይሆናል። እሱ የማለዳ ኮከቡን ያስተዋውቃል። እርሱ የመሲሁ መንገድ ጠራጊ ነው” አለ። እንዴት ሊሆን ይችላል?

170 አንዳንዶች፡ “ምስኪን ሽማግሌ። ኦህ፡ ከ—ጭንቅላቱ ትንሽ የለቀቀ ይመስላል፡ ታውቃላችሁ። የሆነ ትንሽ ነገር አለው። ነገር ግን አረጋዊቷን ኤልሳቤጥን እዚያ ተመልከቷት፡ ሰማንያ አከባቢ ሆናለች። ዘ—ዘ—ዘካርያስን ተመልከቱት፡ በጣም ያረጀ እና የሚንቀጠቀጥ፡ ደግሞ እንደዚህ ያለ ነገር ይናገራል። ደህና፡ ምስኪኑ አዛውንት” አሉት።

171 እሱ ግን የጌታ ቃል ተቀበለ። ለበርካታ ቀናት ራሷን እስክትደብቅ ድረስ፡ እንዲህ ያለ ነቀፌታ ደረሰባት። ይሁን እንጂ ቃሉን ጠብቋል። ኦህ፡ ማይ!

172 ተወዳጅነትን እምቢ አሉ፡ የሕዝብን አስተያየት አልተቀበሉም፡ የዘመኑን ምሁራን አልተቀበሉም፡ የዘመኑን ስታይል እና ሌሎች ነገሮችን አንቀበልም አሉ። አልተቀበሉትም። ከማያምኑ ሰዎች ጋር ለመሄድ ፈቃደኞች አልነበሩም። የዓለምን ነገር እምቢ አሉ። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ተስማምተው ለመኖር፡ ይህን ማድረግ ነበረባቸው። ማድረግ ነበረባቸው።

173 ዛሬም እንደዚያው ነው። ከራሳችሁና ከእግዚአብሔር በስተቀር ከማንኛውም ነገር ራሳችሁን ትለያላችሁ። ቤተ ክርስቲያን የምታደርገው ነገር አይደለም። አንተ ከእግዚአብሔር ጋር የምታደርገው ነገር ነው። አየህ? አንተ ነህ፡ እንደ ግለሰብ የሚታደርገው። አዎን።

174 ነገር ግን እግዚአብሔር ምን እንደሰጠው ተመልከቱ። ኢየሱስ ራሱ ሲመጣ፡ ዘካርያስ ሞቷል፡ ኤልሳቤጥም፡ ጭምር። ነገር ግን ልጃቸው በምድረ በዳ፡ **የሰራዊት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** እያለ ሲመጣ፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “ከሴት ከተወለደው እንደ እርሱ ያለ ታላቅ ሰው የለም።” አሜን። ምን? በመሃንነት ነቀፌታ ተሰቃይታለች። ከቃሉ ጋር ጸናች፡ ከዚያም እንዲህ ያለ ልጅ ወለደች።

175 ልክ እንደ አሮግቷ ሣራ፡ ልክ እንደ ሽማግሌው አብርሃም፡ ሽማግሌዎቹ ጥንዶች ከቃሉ ጋር ተጣበቁ። ተመልከቱ፡ ከተወለዱት ሁሉ፡ “ልክ ባህር ዳር እንዳለው አሸዋ፡” በዓለም ላይ እንደ አይሁዶች ያለ ብዙ ሕዝብ የለም። “እንደ ባሕር አሸዋ ወይም እንደ ሰማይ ከዋክብት።” ምን ሆነ? በጥቂቱ፡ በአንድ ልጅ ሆነ።

176 አሁን ወዴት እንደምሄድ ተመልከቱ። እግዚአብሔር አንድ ልጅ ብቻ፡ እሱን ብቻ ነው የሚፈልገው። አህዛብን ለማናወጥ ወደ መሢሑ ለመጠቆም አንድ ልጅ ብቻ አስፈለገው። አንድ ታዛዥ ልጅ፡ ወሰደ። በትክክል። እግዚአብሔር አንድ ሰው ብቻ ይፈልጋል። የሚያስፈልገው ይህ ብቻ ነው፡ የሆነ ቦታ ድምፁን

ማሰማት ከቻለ ያንን ነው በቃ። እሱ የሚፈልገው ያንን ብቻ ነው፡ አንድን ሰውን በቁጥጥሩ ስር ማድረግ። ኦህ፡ አንድ ሰው ማግኘት እንዴት ይወዳል!

177 አንድ ጊዜ፡ ኖኅን አገኘ። አ—አንድ ጊዜ፡ ሙሴን አገኘ። አ—አንድ ጊዜ ኤርምያስን አገኘ። ኤ—ኤልያስን አገኘ። ኤልሳዕን አገኘ። ዮሐንስን አገኘ። አ—አገኘ... ሳምሶንን አገኘ። አንድን ሰው በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ እስከቻለ ድረስ፡ ይህ ድምፁ ነው። በዚያ ሰው አማካኝነት መናገር ይችላል። ዓለምን ሊኮንን ይችላል። ኦህ፡ ማይ!

178 ሰው በቁጥጥሩ ሥር እንዲገባ፡ እንዴት እንደሚራብና እንደሚወጣ፡ "በእርሱ በኩል መናገር እችል ዘንድ፡ ድምጼም እንዲታወቅ ለማድረግ። ምንም እንኳ ነቀፌታ ቢደርስበትም፡ ድምጼ እንዲታወቅ አደርጋለሁ።" እያችሁ? ኦህ፡ አዎን።

179 በመጀመሪያ፡ መሃንነት። መሃን መሆን ነበረባት፡ መሃንነት የሚያስከትለቀ ነቀፌታ መቋቋም ነበረባት። ሣራ መቋቋም ነበረባት። ዘካርያስና ኤልሳቤጥም እንዲሁ መቋቋም ነበረባቸው።

180 ተመልከቱ፡ ዛሬ። ዛሬ አንድ ነገር እላችኋለሁ። ዛሬ የጋለሞታዋ ልጆች ተመልከቱ። ይህች ጋለሞታና ሴቶች ልጆቿ፡ ዓለማትን በሙሉ በሃይማኖት ተቋም በፖለቲካዊ አገዛዝ ሥር አድርገዋል። የሃይማኖት ተቋም ትውልድ ምን ያህል እንደ ተነሡና፡ ጻድቃን ምን ያህል ጥቂት እንደሆኑ ተመልከቱ። አትጨነቁ። ከቃሉ ጋር ተጣበቁ። ችግር የለውም።

181 ሊሳለቁባችሁ፡ ሆሊ-ሮለር ልትባሉ ትችላላችሁ። ማንኛውም ዓይነት፡ መጥፎ ሰም ሊሰጧችሁ ይችላሉ። ነገር ግን፡ እዚያው ቆዩ፡ ይህ ቃል ነው፡ ስለእናንተ የሚናገሩት ነገር፡ ያ የቃሉ ነቀፋ ነው።

182 አንድ ወጣት፡ ምናልባት በዚህ ጠዋት እዚህ ሊሆን ይችላል። ወዳጄ ነው፥ ጂም ፑል ይባላል፡ ወጣቱ ጂም፡ ሕ—ሕዝቡም ጭምር። በቀደም ተጠይቆ ነበር። እና፡ እዚህ ተጠምቋል። አንድ ሰው፡ እንዲህ አለው፡ "በቤተክርስቲያን ውስጥ ለመጠመቅ ከፈለግክ፡ ለምን ትልቅ ቤተክርስቲያን ወይም ሌላ ነገር፡ አትፈልግም? እያችሁ? እርሱ ግን ብርሃኑን አይቷል። ያ ነበር። እያችሁ?

183 "ከጻድቃን ይልቅ የኃጢአተኞች ልጆች ይበዛሉ።" አዎን። ችግር የለውም። በኖኅ ዘመን የነበሩት፡ ጻድቃን ምንኛ ጥቂቶች ነበሩ! በኖኅ ዘመን የነበሩት ሰዎች ምን ያህል ጥቂት እንደነበሩ ተመልከቱ። እያችሁ? በሰዶም ዘመን የነበረውን ሁኔታ ተመልከቱ። እያችሁ? ጻድቃን ምን ያህል ጥቂት ናቸው!

184 አመንዝራዋ ምን ያህል ልጆች አሏት! በማነኛውም በአሮጌ መንገድ ልጆቿን ታሳድጋለች፡ ነገር ግን ሁሉም ልጆቿ ዲቃላ ናቸው። ጋለሞታይቱ ጋለሞታይቱን ትወልዳለች። ውሻው ውሻውን ይወልዳል።

185 ክርስቶስም የተቀባውን ይወልዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ጻድቃንን ይወልዳል፡ ስለዚህ ምስኪን መንጋ የመሆን ሃሳብን መቋቋም አለብን። እንዴት ያለ ግሩም ስጦታ ነው!

186 ታላቁን የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ተመልከቱ፡ አሥራ ሁለት ብቻ ነበሩ። አዎን። ከእነሱ ጐን፡ ዛሬ ምን ዓይነት ቡድን እንዳለን ተመልከት። አዎን።

በኖኅ ዘመን ስምንት ነፍሳት ብቻ ነበሩ።

187 በሎጥ ዘመን አምስት ብቻ ነበሩ፡ ማለቴ፡ አራት፡ ሎጥና ሚስቱ፡ ሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ብቻ ነበሩ። እሷም ከወጣች በኋላ፡ ወደ ኋላ በማየቷ የጨው አምድ ሆና ቀረች። በእውነቱ፡ በዚያን ቀን ሶስት ብቻ ወጡ።

188 ኢየሱስም ሲናገር፡ "በዚያ ዘመን እንደነበረው ሁሉ" ብሏል። እኛም ነቅተን መጠንቀቅ አለብን። ጻድቃን ምንኛ ጥቂቶች ናቸው! ነገር ግን፡ እንደ ሁልጊዜም፡ ፌዘኞች መንቀፋቸው አይቀርም። በ-... መጀመሪያ፡ መካንነትን ነቀፌታ ተቋቋሙ። ማይ!

189 ቶሎ ማለት አለብኝ። እ... እ... እነዚህን ሕፃናት መርዳት እፈልጋለው። ትንሽ ግዜ ብቻ ታገሡኝ። አያችሁ?

190 ሰዎች ሁሌም እንደድሮው ናቸው። አሁን አንድ ነገር በድጋሚ እላለሁ። ይህ ሰብከት እ... እየተቀዳ ይሁን፡ አይሁን አላውቅም። ነገር ግን በቴፕ ላይ ከተቀዳ፡ በቴፕ ላይ የምታዳምጡት፡ እንድታዳምጡኝ እፈልጋለሁ። እንዳያመልጣችሁ፡ ነገር ግን አጥኑት። አሁንም ሰው ዘወትር እንደ ድሮው ነው። እግዚአብሔር ስላደረጋቸው ነገሮች እግዚአብሔርን ያመሰግናል፡ ወደፊት ስለሚያደርጋቸው ነገሮች በጉጉት ይጠባበቃል፥ አሁን ስላደረጋቸውና እያደረጋቸው ስላሉት ነገሮች ግን ችላ ይላል። እግዚአብሔርን ስላደረገው ነገር ያመሰግነዋል፡ ወደፊት ለሚያደርገው ነገር በጉጉት ይጠባበቃል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን ነገር ችላ ይላል፡ እዚያ ጋር ነው ሙሉውን ነገር የሚያጣው። ተረድተዋል ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ። አያችሁ? አሁን የሚሰራውን ነገር ችላ ይላል! ሰው እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር ያውቃል፣ ወደፊት የሚያደርገውንም ቃል የገባውን ነገር ያውቃል፣ ሆኖም አሁን የሚያደርገውን ነገር ማየት ያቅተዋል።

191 ኦህ፡ እናንተ የጴንጤ እምነት ተከታዮች፡ ለዚህ ምሳሌ አይደላችሁምን! ሁልጊዜው፡ ወደፊት አንድ ነገር እንዲሆን በጉጉት ትጠባበቃላልችሁ፡ ፊታችሁ ይህን ተፈጽሟል፡ እናንተም አላወቃችሁትም። "ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምታቅፍ እግዚአብሔር ምን ያህል ጊዜ ሊያቅፋችሁ ፈልጎ ነበር፡ እናንተ ግን አልፈለጋችሁም።" ከቃሉና ከመንፈሱ ይልቅ ለትውፊታችሁና ለሃይማኖታችሁ ተቋም ትልቅ ቦታ ሰጣችሁ። አዎን።

192 ለማርያም እንዴት ያለ ነቀፌታ ነው! (እየዘጋን ነው።) ለቃሉ ሲሉ ማርያምና ዮሴፍ፡ እንዴት ያለ ነቀፌታ ነው! የክሪስማስ ወቅት ነው። ትንሽ ስለ ክሪስማስ ማውራት አሰቤ ነበር፡ ነገር ግን ከሬዲዮና ከፓስተሮችና ወዘተ፡ ብዙ ትሰማላችሁ። ማርያምና ዮሴፍ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠበቃቸው ምንኛ ነቀፌታ ደርሶባቸዋል! አሁን፡ አስታውሱ። ንቀታቸውም፡ ቅንድባቸውን ወደላይ አድርገው፡ ምስኪኗ ማርያም ስታልፍ ሲያዩ፡ ዮሴፍን ሲያዩ ይንቃሉ። "ሴተኛ አዳሪ እያገባ ነው።" አያችሁ? እና ልብበሉ፡ ወንድሜ፡ አመንዝራነት ያኔ ሞት ነበር። "አሁን፡ እንዳትገደል እርሷን ጠብቅ። ከአንተ የተነሣ እናት ትሆናለችና።" እና፡ ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ ሁሉ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር እየተገናኘ ነበር፡ ያም እንደቃሉ መሠረት ነበር። እነሱም ይህን አላወቁም። አያችሁ?

193 "ድንግል ትጸንሳለች።" ዮሴፍ ይህን ያውቃል። ማርያም ይህን አውቃለች፡ ምክንያቱም፡ መልአኩ መጥቶ፡ ቃሉ ከተፃፈ በኋላ፡ ሊሆን ያለውን ነገር፡ የተጻፈውን ቃል ሁሉ እየገለጠላቸው፡ ወይም እያረጋገጠላቸው ነበር። አሁን

አታልሙ። አሰቡ። መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር ወረደ፥ ለሁሉም ጉባኤ ፈጽሞ አልተናገረም። ለእነርሱ ብቻ ተናገረ።

194 ዮሴፍ ተመለከተ። መልአኩ ሊጎበኘው ከመምጣቱ በፊት፡ እንዲህ አለ፡ “እንግዲህ፡ እኔ አሁን፡ እወዳታለሁ። ግን፡ እኔ ጻድቅ ሰው ነኝ። እንደዚህ ያለች ሴት ማግባት አልችልም።”

195 የጌታ መልአክም፡ በሕልም ተገለጠለትና፡ እንዲህ አለው፡ “የዳዊት ልጅ፡ ዮሴፍ ሆይ፡ እጮኛህን ማርያምን ወደ ቤትህ ለመውሰድ አትፍራ፡ የፀነሰችው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና።” ኦህ፡ ማይ! ምንኛ የሚያጽናና ነው! አያችሁ?

196 እና፡ ማሪያም፡ ወደ ውሃ ጉድጓድ ስትሄድ። ምስኪን ድንግል፡ አሥራ ሰባት ዓመት ገደማ፡ አሥራ ሰምንት አከባቢ ሆና፡ ከዚህ በፊት ተጋብቶ አራት ልጆች ያሉትን፥ አንድ ሽማግሌ ታገባለች። እ... እሷም ወደደችው፡ ለ—ለምን እንደሆነም አላወቀችም። እሱም ወደዳት፡ ለምን እንደሆነም አላወቀም። እንዲህ ነበሩ። ወደ ጉድጓዱ እየመጣች፡ ውኃ ለመቅዳት፡ እየሄደች፡ ያለ ጥርጥር፡ ቅዱሳን መጻሕፍትን፡ ያ—ያጠናችውን ነገር እያሰበች ሳለች፡ ብርሃን በፊቷ ላይ በራ። ያ ብርሃን ሲበራ፡ መልአክም እዚያ ቆመ።

197 ምስኪን ማርያም ምን ተሰምቷት ይሆን? አሰባችሁ ታውቃላችሁ? ትናንት እኔ እንደፈራሁ ተሰምቷት ይሆን ብዬ አሰባለሁ።

198 “ሄይል፡ ማርያም!” **ሄይል** ማለት “እነሆ” ነው። “ለሚነግርሽ ነገር ትኩረት ሰጪ ነው። ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፡ በአምላክ ፊት ሞገስን አግኝተሻልና፡ ልጅም ትወልጃለሽ። ምንም ወንድ ሳታውቂ፡ ልጅ ትወልጅያለሽ። የአጎትሽ ልጅ ኤልሳቤጥም፡ በዕድሜዋ አርጅታለች፡ እርሷም፡ አርግዛለች፡ ልጅም ትወልዳለች። እነዚህ ምልክቶችም ይፈጸማሉ።”

ማርያምም አለች፡ “እኔ ወንድ፡ አላውቅም፡ ታዲያ ይሄ እንዴት ሊሆን ይችላል?”

199 እርሱም፡ “መንፈስ ቅዱስ ይጸልልሻል። ስለዚህ የሚወለደው ቅዱስ ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።”

200 ፌዘኞቹ የፈለጉትን ይበሉ። እሷም አወቀች። እሷም እንደሚሆን ታውቅ ነበር፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ብሏልና።

201 አሁን፡ እንደዚህ ይዛ ስትሄድ፡ በዚያ ልጁን አደራ በሚሰጥበት፡ ወይም ህጻኑ በሚገረዝበት ጊዜ፡ **ይህን** ትንሽ ሕፃን በእጆቿ፡ ደግሞ እንዴት ተሰምቷት ይሆን። ሴቶች ሁሉ ርቀታቸውን ከእርሷ ጠብቀው፡ ሁሉም የክት ልብስ ለብሰው፡ ሕፃናቶቻቸውን ለመስጠትና እንዲገረዙ ለማድረግ፡ ሁሉም ማለት ይቻላል በግ እየጐተቱ ነበር የሄዱት። እሷ ግን ራሷን ለማንጻት፡ ሁለት ርግቦችን ይዛ ገባች። ህጻኑ በመጠቅለያ ተጠቅሏል፡ የመጠቅለያ ልብሱም የተሰራው በበሬ አንገት ላይ ቀንበር ሲደረግ፡ ቀንበሩ፡ አንገቱን እንዳይበላው ከሚደረግ መጠቅለያ ነው። ያም በበረት ውስጥ ለከብቶች ምግብ የሚሰጥበት ማሰሪያ ልብስ ነው። ለእሱ የሚያቀርቡለት ምንም ነገር አልነበራቸውም። በጣም ድሆች ነበሩ። እርሷም ቆመች።

202 ሴቶች ሁሉ ከምስኪኗ ድንግል ርቀታቸውን መጠበቃቸው፡ አያጠራጥርም። እንዲህ እያሏት፡ “እያችሁ፡ ልጇ ዲቃላ ነው።” እግዚአብሔር

ነገሮችን እንዴት የተለየ-አድርጎ እንደሚያሳያቸው ተመልከቱ። ኦህ፡ ማይ! እሱ የሰይጣንን አይን እንዴት እንደሚያሳውረው ተመልከቱ። ምን ያህል አስጸያፊ ነው! ምን ያህል ቆሻሻ ነው! ምንዝርና። እሷም እንደዚያው ናት። አመንዝራ ናት።" ይህ ግን በምስኪኗ ማርያም ልብ ውስጥ ያለውን የልብ ምት አላቆመም። ከእርሷ ርቀታቸውን ጠበቁ።

203 እነሱ አሁንም ተመሳሳይ ነገር እያደረጉ ነው፡ አሁን እርሱን፡ "ሆሊ-ሮለር፡ ወይም አክራሪ፡" ወይም የሆነ ነገር ይላሉ።

ማርያም ያ ሕፃን የማን እንደሆነ ታውቃለች። እሷም እንደ ቀድሞው፡ ቀጠለች።

204 ነገር ግን፡ ኦህ፡ ከኋላው ባለው ክፍል ተቀምጦ የነበረው ሰው፡ ስምዖን፡ ቃል የተገባለት መሆኑን አላስተዋልምን? ትንቢት እየተናገረ፡ ዞረ። እንዲህም አለ፡ "ጌታ ተገለጠልኝ።" እርሱም፡ በወቅቱ ዕድሜው ሰማንያ-ዓመት ገደማ ነበር፡ እና "ሞትን አልሞትም… " አላቸው። "የእርሱን መዳን ሳላይ ሞትን አላይም" አላቸው።

205 "ኦህ፡ ስምዖን ሆይ፡ ሸምግለሃል፡ ልጄ። ሸ—ሸ… ሸማግሌው መርሳት ጀምሯል፡ ታውቃላችሁ፡ እርሱ ትንሽ… ተውት በቃ። ጉዳት አልባ ነው። ማንንም አይጐዳም።"

206 ስምዖን ግን የጌታ ቃል ነበረው፡ እንዲህም አለ፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ሲወርድ አየሁ። ቆም ብዬ ተመለከትኩት። እርሱም፡ 'ስምዖን፡ አንተ ጻድቅ ሰው ነህ። በዚህ ነገር ላይ ምስክር አደርግሃለሁና… አንተ አትሞትም።'" ኧሃ-ሃህ። ያ ነው።

"ጌታ ሆይ፡ ይህን የምታደርገው ለምንድን ነው? "

"ይህ የእኔ ስራ ነው።"

207 እንደሚመስለኝ፡ በዚያን ቀን፡ በላያቸው ላይ ፍም እንደሚያፈስባቸው አስባለሁ። "የሚመሰክርላችሁ ነበራችሁ። ለምን አልሰማችሁትም?

208 አሮጊቷ ዓይነ ስውር ሃና፡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ተቀምጣ፡ እየጸለየች ነበር። ጌታም ገለጠላት፡ "ስምዖን ትክክል ነው" አላት። አሜን። ጨለማ እና የቀን ብርሃን ለይታ ማየት አትችልም ነበር፡ ነገር ግን እሷ በዛሬው ጊዜ ጥሩ ዓይኖች ያላቸው ብዙ ሰዎች ከሚያዩት በላይ አየች። የመሲሁ መምጣት እንደተቃረበ፡ በመንፈስ፡ አየች፡ መንፈሱም በልቧ ውስጥ ተንቀሳቀሰ።

209 ምን ዓይነት አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን እንደነበረች አይታችኋል? ዘካርያስ፡ ኤልሳቤጥ፡ ማርያም፡ ዮሐንስ፡ ሃና፡ እና ስምዖን፥ ከብዙ ሚሊዮን መካከል ስድስቱ። ልክ በኖኅ ዘመን እንደነበረው። ስድስቱ። እግዚአብሔር ከእያንዳንዳቸው ጋር ይነጋገራል። ሁሉም አንድላይ ነበሩ። ሁሉም አንድ ላይ ተሰበሰቡ። አሜን።

210 እዚህ ጋር፡ ሽማግሌው ስምዖን። እዚህ ጋር ሕፃኑ ገባ። ከዚህ በፊት ስለዚህ ጉዳይ ሰምቶ አያውቅም። ሕፃኑ ይኸው መጣ። ከዚያም ስምዖን በክፍሉ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ፡ መንፈስ በእርሱ ላይ ወረደ፡ እንዲህም አለው፡ "ስምዖን ሆይ፡ ውጣ" አለው።

211 እነሆ እየተራመደ፡ ወጣ፡ የት እንደሚሄድ አያውቅም። ልክ እንደ አብርሃም፡ አንድ ነገር እየፈለገ ነበር። የት እንዳለ ባያውቅም፡ መንቀሳቀሱን ቀጠለ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም፡ ቆመ። መንፈስ ቅዱስም እንዲህ አለው፡ “ይሄውና እርሱ ይህ ነው።”

212 ደርሶ፡ እጁን በማርያም እቅፍ ዘርግቶ፡ ሕፃኑን በእጁ አቀፈው። ወደ ላይ ቀና ብሎ ተመለከተና እንዲህ አለ፡ “ጌታ ሆይ፡ ባሪያህ ከዚህ ህይወት በሰላም ይሂድ። ዓይኖቼ ማዳንህን አይተዋል።” ሁሉም እየሳቀበት የነበረውንና፡ ሴቶቹም እየሸሹት የነበረውን ነገር፡ ስምዖን፡ “ጌታ ሆይ፡ ይህ ያንተ ማዳን ነው” አለው።

213 በዚያን ጊዜ፡ እነሆ አንዲት አሮጊት ዓይነ ሰውር ሴት መጣች፡ በጉባኤው መካከል እየተንከራተተች፡ እየዞረች መጣች። እሷም ወደ እሱ ቀረበች፡ እሷም ትንቢትን ተናገረች፡ ምክንያቱም እሱን እየፈለገች ነበር። ማርያምን እንዲህ አለቻት፡ “ሰይፍ በልብሽ ውስጥ ያልፋል፡ ነገር ግን የብዙዎችን ልብ ሃሳብ ይገልጣል።” አያችሁ? ያ ምን ነበር?

214 አሁን፡ ከእነዚህ ሴቶች መካከል አንዳንዶቹ፡ እንዲህ ያሉ ይመስለኛል፡ “አሁን ያንን ተመልከቱ! ምን አይነት የሰዎች ሰብሰብ ነው? ይሄውላችሁ። አያችሁ? ያ ነው። ከማን ጋር እንዳለ አያችሁት? ሽማግሌው ሰውዬ፡ አእምሮው ሰቷል። ይሄው፡ ከዚያች ዝሙት አዳሪ ሴት ፊት ቆሞ፡ እንዲህ ዓይነት ነገር ይናገራል። ይሄውላችሁ። ያን ዲቃላው ልጅ። አሮጊቷን ሃናን ተመልከቷት፡ እዚህ ቁጭ ብላ፡ እንደዚህ እየሄደች፡ ራሷን በረሃብ ገደለች። እንደ እኛ ምንም አትደሰትም። ነገር ግን፡ ይሄው እንዲህ ናት፡ አያችሁ። የሀገሪቱ ማህበራት በሙሉ አባል ልትሆን ትችላለች። በጣም ጥሩ ከሆነ ቤተሰብ ነው የመጣችው፡ አያችሁ፡ የዚህ አባል መሆን ትችላለች። ነገር ግን ተመልከቷት። እነዚህ ሰዎች እንዴት አንድ ላይ እንደሚሰባሰቡ አይታችኋል? ኦህ፡ አዎን። አሜን።

215 ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ነው። “በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ሰፍራዎች ተቀምጠናል፡ በመንፈስ ቅዱስ ከፍ ከፍ ተደርገናል።” እርግጥ ነው። እዎ፡ ወዳጄ።

216 ኦህ፡ ትንሽ ተጨማሪ ጊዜ አለን? የሆነ ነገር መናገር አለብኝ። [ጉባኤው፡ “እዎን” አለ።—አርታዒ።]

217 እዚህ ሌላ ገጸ ባህሪ አለ፡ እያየሁት ነው፡ ያን ጊዜ ቃሉ በተገለጠበት ወቅት፡ የነበሩ ሰብአ ሰገል ናቸው።

218 ፍሬድ፡ ይህን ለማንበብ፡ ጊዜ ቢኖረኝ ደስ ባለኝ ነበር። ኪስህ ውስጥ ይዘኸዋል? [ወንድም ፍሬድ ሶትማን፡ “እዎን” አለ።—አርታዒ።] ብዙዎቻችሁ በመጽሔቱ ላይ እንዳያችሁት እገምታለሁ።

219 ከሰላሳ-ሶስት ዓመታት በፊት፡ መንፈስ ቅዱስ እዚህ ወንዝ ላይ የተናገረውን ነገር፡ ፈልፍለው አውጥተውታል። ታኅሣሥ 9፡ ያንን አስትሮኖሚ በማረጋገጥ፡ ያ ጁፒተርና እ—እነዚያ ከዋክብት፡ እንዴት በህብረት እንደተቀመጡ!

220 የ-... ድሮ የሥነ ከዋክብት ምልክቶችን አገኙና፡ ፈልገው አገኙት። እነዚህ ከዋክብት፡ በኮከብ ኮንስታሌሽን ውስጥ ገብተው፡ ወደ ባቢሎን በቀጥታ

ተወረወሩ፡ ጠቢባኖቹም እንደገና አመጡት። አስታወሳችሁ? በቢሊዮኖች የሚቈጠሩ፡ የብርሃን ዓመታት ርቀት ላይ፡ እንደገና ተሻግረዋል። በባቢሎን የነበሩት እነዚያ የአይሁድ ጠቢባን፡ እነዚያን ከዋክብቶች፡ ኮንስታሌሽን ወደ ከዋክብት ኮንስታሌሽን ሲመጡ አዩ። ሦስቱ አንድ ላይ ተንቀሳቅሰው፡ አንድ ሲሆኑ፡ የንጋት ኰከብ ይሰራሉ። እነዚህ ሰዎች፡ ከዋክብት አንድ ላይ የሚሰባሰቡበት ጊዜ እንደሆነና፡ መሢሑ በምድር ላይ እንደሚገለጥ፡ ያወቁት ከእግዚአብሔር ቃል ነው።

221 ለዚህም ነው እንዲህ ማለት የጀመሩት፡ "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ፡ የት አለ? የት አለ? የሆነ ቦታ! ምክንያቱም፡ እነዚህ ከዋክብት ሲመጡ፡ የሰማይ አካሎቻቸው ወደዚህ ታላቅ የሰማይ አካል እስኪቀየሩ ድረስ፡ ሦስቱም አንድ ላይ ሲንቀሳቀሱ፡ በዚያን ጊዜ መሢሕ በምድር ላይ ይሆናል" አሉ። ከዋክብቶቹ ወደ ምህዳራቸው ሲንቀሳቀሱ፡ እነዚያ ሰዎች መሢሕ በምድር ላይ መሆኑን አወቁ።

222 በዘርፉ የተካኑ ባለሙያዎች ነበሩ። ታላላቅ ሰዎች ነበሩ። በሃይማኖት ሳይንስ መስክ የተካኑ ባለሙያዎች ነበሩ። ሃይማኖታዊ ገጽታውን እየተመለከቱ ነበር። እነዚህ ከዋክብት ጁፒተር እና ሳርጋስ፡ ከአድማስ ባሻገር ሲንቀሳቀሱ ተመልክተዋል፡ ከ—ከዚያም ወደ መስመሮቻቸው ይንቀሳቀሳሉ። እነሱም እንዲህ አሉ፡ "መሲሑ አንድ ቦታ እንዳለ እናውቃለን። ስለዚህ፡ እርሱ በኢየሩሳሌም መሆን አለበት፡ ምክንያቱም ያ የዓለም ሃይማኖት፡ የመሲሁ ሃይማኖት ዋና ቦታ ነው። ይህ የእነሱ ዋና መሰሪያ ቤት ነው። የሃይማኖት ተቋም ዋና መሰሪያ ቤት ነው። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ቡድን የሚቀመጠው እዚያው ነው" አሉ።

223 ግመሎች ላይ ተቀምጠው፡ ለሁለት ዓመት ያህል፡ የጤግሮስ ወንዝ አቋርጠው፡ ረግረግና በጫካዎች በኩል፡ እየተጓዙ፡ ወደ ከተማዋ ሰሄዱ፡ ልባቸው በደስታ ተሞልቷል።

224 እነዚህ ከዋክብት በዚያ ላይ ተንጠልጥለው ሲያዩ አወቁት። ይህም፡ የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች እንዲህ ይላሉ፡ ዛሬም፡ "በእውነቱ፡ እነዚያ ከዋክብት፡ እንደገና ወደዚያ ቦታ ቢመጡ፡ ከቆሙበት፡ ሲታዩ፡ አንድ ኰከብ ይፈጥራሉ።" ነገር ግን ይህን ለማየት፡ በቦታው ላይ መቆም ነበረባቸው። አሜን። አሜን።

225 በየትኛው አቅጣጫ እንደምትቆም ይወሰናል። ምን እየተመለከትክ እንደሆነ በዚያ ይወሰናል። ኧሃ-ሃህ። አዎን።

226 ስለዚህ አዩት፡ ተከተሉት፡ እነሱ በሰፍራቸው ላይ ነበሩ። የትም ቢገቡ፡ ከእነርሱ ጋር አንድ ላይ ነበር። ይመራቸው ነበር። አያችሁ?

227 በዚህ መንገድ ነው ቅዱሳት መጻሕፍትን ሁሉ ማቀናጀት ያለባችሁ፡ ሁሉንም ነገር፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር የጸኑ ሆኑ። ይህ ብቸኛው መንገድ ነው። በቀጥታ ወደ እሱ ያደርሳችኋል። በእርግጠኛነት ያደርሳቸዋል።

228 አሁን ልብ በሉ። "የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ፡ ወዴት ነው? " እያሉ፡ እየተናገሩ መጥተው፡ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገቡ፡ ኮከቡ በቀጥታ፡ ወደ ሃይማኖት ተቋም ዋና መሰሪያ ቤት ወሰዳቸው። ከዋክብቱንም ያዩ ዘንድ ዞሩ፡ ወዲያውኑም ኮከቡ ተለያቸው። ወደ ከተማው ገቡ፡ በጐዳናው ላይ-እና-ታች አሉ። ከተማዋ በእግዚአብሔር ደስታ ትሞላለች ብለው አሰበው ነበር። በመንገድ ላይ-እና-

ታች እያሉ፡ በደስታ፡ መጡ፡ እየጮኹ፡ “የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? በምሥራቅ ሳለን ኮከቡን አይተን፡ ልናመልከው መጥተናልና” አሉ።

229 አስታውሱ፡ ኮከቡ፡ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ተጓዘ። እነሱም በምሥራቅ ነበሩ። “ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እያመራ፡ አሁንም እየቀጠለ ነው። እኛንም እየመራ ነው... ” አያችሁ? እነሱ በፍጹም... እነሱ... ደሳና፡ ባቢሎን እና ህንድ የሚገኘው ከፍልስጤም በስተ ምሥራቅ፡ በደቡብ ምሥራቅ ነው። ወደ ምዕራብ አቅጣጫም እየተጓዙ ነበር። “በምዕራብ አቅጣጫ፡” “አሁንም ይቀጥላል። ወደ ፍጹም ብርሃን ምራን፡” የሚለውን ዝማሬ ታውቁታላችሁ። አያችሁ? እነዚያ፡ ጠቢባን፡ ወደ ምዕራብ እየመጡ ነበር። ምሥራቅን ትተው፡ ወደ ምዕራብ በመሄድ፡ ኮከቡን አዩት። አሁን፡ በምዕራቡ ውስጥ ሆነው፡ ወደ ኋላ ቢመለከቱ፡ አያዩትም። አያችሁ?

230 ወደዚያ፡ በደረሱ ጊዜ፡ ወደዚያ መራቸው፡ ከዚያም ትቷቸው ሄደ። እነሱም እንዲህ ብለው አሰቡ፡ “ይሄው። ኰከብ ሄዷል፡ ስለዚህ እዚህ ነው” አሉ። በከተማ ነበሩ። ስለዚህ፡ “ኦህ፡ ማይ፡” እንዲህ አሉ፡ “ሁሉም ሰው እየዘመረና ደስተኛ ነው። የእግዚአብሔር ክብር ሁሉንም ነገር አብርቷል። ስለዚህ፡ እዚህ ነን። እኛ ያ—ያለንን ሰኬት እናውቃለን፡ ያንን ኮንስታሌሽን ሰንመለከት፡ ማንም፡ ማንም ጌታ፡ እዚያ መጥቶ እነዚያን ከዋክብት አንድ ላይ መሳብ አይችልም። ይህን ደግሞ እናውቃለን፡ ከ—ኮከቦቹ ወደዚያ ሰማያዊ አካል ሲመጡ፡ ያ ጊዜ ነው መሢሑ በምድር ላይ መሆኑን እናውቃለን። መሢሑ በምድር ላይ ነው።”

231 በየብዙ መቶ ዓመታት፡ ኰከቦቹ ኮንስታሌሽናቸውን በድጋሚ ያልፋል፡ አያችሁ፡ ያን ጊዜ ሰጦታ ወደ ምድር ይመጣል። ልብ በሉ።

232 “የከዋክብት ሰብሰብ አንድ ላይ ሲሰባሰቡ፡ መሢሑ በ—በምድር ላይ ይሆናል።” እነርሱም መምጣቱን አውቁ፡ ስለዚህ ወደ ሃይማኖቱ ዋና መሰሪያ ቤት ሄዱ፡ መሄድ ጀመሩ፡ በየመንገዱ ወደላይ እና ወደ ታች እያሉ፡ በእነዚህ ግመሎች ላይ ተቀምጠው፡ እንዲህ እያሉ፡ “እርሱ የት አለ? የት ነው ያለው? የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተናል። እዚህ የሆነ ቦታ አለ። የት ነው ያለው? የት ነው ያለው? የት ነው ያለው? ” ኧሃ! እንዴት ያለ ነቀፌታ ነበር!

233 ከዚያም ወደ ሊቀ ካህናቱ ሄዱ። እርሱም፡ እንዲህ ብሎ ይሆናል፡ “እናንተ ሰዎች ችግራችሁ ምንድን ነው? እንዴ፡ እናንተ አክራሪዎች!” አያችሁ? እንዴት ያለ ነቀፌታ ነው፡ ከሳይንሳዊ ግኝታቸው! በእግዚአብሔር ኃይል፡ የእርሱን ኰከብ አዩ። እነሱ ጥበበኛ ሰዎች ነበሩ፡ ብልህ ነበሩ። በሃይማኖት ሳይንስ መሰክ ውስጥ ነበሩ። ከዋክብቱ፡ በዚያ በደረሱ ጊዜ፡ መሢሑ በሆነ ቦታ እንዳለ አወቁ። እዚህ ጋር፡ ይህ ነገር መታወቅ በነበረበት ሰፍራ ላይ፡ አንዳች ነገር አልታወቀም።

234 በመንገድ ዳር ላይ የቆሙ ልጆች፡ እንዲህ ሲሉ፡ ይታዩኛል፡ “ሃ! ይህን ተመልከቱ። ሃ! እነዚህ አክራሪዎች። ‘የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ፡ ወዴት ነው፡’ ሲሉ፡ ሰማችኋቸው? የዚህ አካባቢ ንጉሥ ሄሮድስ እንደሆነ አያውቁም። ቢሾፕ **እከሌን** አያውቁትም።” ኦህ፡ ማይ!

235 “የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የት አለ? በምሥራቅ ኮከቡን አይተናልና።”

236 እነርሱም፡ “እናንተ የጥበብ ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁም፡ ወደዚህ ተሰብሰቡ።” ኧሃ-ሃህ። “ወደዚህ ቅረቡ። ሁላችሁም በሆነ ቦታ ላይ አንዳች ኮከብ አይታችኋልን? ”

“ኦህ፡ እንደዚህ ያለ ነገር አይቼ አላውቅም።”

237 “ሁላችሁም የሥነ ከዋከብት ተመራማሪዎች ወደዚህ ቅረቡ። ሁላችሁም በሆነ ቦታ ላይ አንዳች ኮከብ አይታችኋልን? ”

“አይ፡ አላየንም።”

“ማንኛውም ዓይነት ምሰጢራዊ ምልክት የሚመስል ነገር ይታያችኋል? ”

“አይ። እንደዚህ ያለ ነገር አላየንም። አይ።”

238 አሁንም፡ አያውቁም። ተመሳሳይ ነገር። ምንም ነገር አያዩም። ሊያዩት አይችሉም።

“እስኪ፡ አገልጋዮችን እ—እንጥራቸው። እናንተስ ምን ትላላችሁ? ”

“አይ። እኛም ኮከብ አላየንም።”

239 “እሺ፡ እናንተ ግንብ ላይ ያላችሁ፡ ጉበኞችስ? እስኪ ከዋክብቱን ተመልከቱ። እናንተ... በሰማያት ውስጥ ኮኮቦች ያሉበት እያንዳንዱ ኮንሰታሌሽን እናንተ ታውቃላችሁ። እያንዳንዱን ኰከብ ታውቃላችሁ። የሆነ ነገር ይታያችኋል? ”

“አይ። ምንም ነገር አላየንም” አሉ። ግን΄ኮ እዚያ የነበረ ነገር ነው።

240 እግዚአብሔር ይመስገን! ኦህ፡ ማይ! አይታያችሁምን? አሁንም አለ፡ ማየት ግን አይችሉም። እየሆነ ያለው፡ በዙሪያቸው ሲሆን፡ እነሱ ግን ሊያዩት አይችሉም።

241 “አይ። እኛ ምንም አላየንም። ኦህ፡ ወደዚያ ሄጄ ነበር። ምንም አላየሁም።” አዎን፡ አታዩም። እጅግ ታውራችኋል። ይህን ለማየት አልተሰጣችሁም። አያችሁ? ይህን ያህል ዕውር ከሆናችሁ፡ ለምን፡ አዎን፡ ይህን ማየት አይቻላችሁም።

242 ያ የተሰጠው እግዚአብሔር ለገለጠላቸው ብቻ ነው። የሚያየው ያ ሰው ነው። ሁሌም እንደዚያ ነበር። በእርግጠኝነት።

243 ዝናቡን በሰማይ ላይ ማየት የቻለው ኖህ ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ የተቀሩት ግን ይህን ማየት አልቻሉም። አያችሁ? ዝናቡን አላዩትም፡ ኖህ ግን አየ።

244 ሣራ ሕፃኑን መያዝዋን ያየ አብርሃም ነበር። ያ ትክክል ነው፡ “የሕዝቦች አባት ሆይ፡ አሁን ስንት ልጆች አሉህ? ” ሲሉት የነበሩ ፌዘኞች አላዩትም።

245 በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን፡ ጠቢባን እና ነብያት፡ ማየት እንችላለን! “እምነት ለማይታዩ ነገሮች ማሰረጃ ነው።” ቃሉ እንደተናገረ ያውቃሉ፡ ይኸው ነው። ማሰረጃው **ይህ** ነው። አይተውታል። አሁን አስተውሉት። ኦህ፡ ማይ!

“ጥበበኞቻችን ኮከቡን አላዩትም። ምንም አይታወቅም።”

246 ለምን? በእውነቱ፡ እየፈለጉ ሳሉ፡ እንዲህ ካሉ አይነት ሰዎች በደረሱ ጊዜ፡ ኮከቡ ጠፋ።

247 ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ነው። ብልጭልጭ የበዛበት ነገር የሚበዛው በዚህ ምክንያት ነው፡ በትክክል፡ መሰረታዊ ችግሩ፡ እምነት አልባ ከሆኑ፡ እንዲህ ካሉ አይነት ሰዎች መገናኘት ነው። የ—የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት እንዴት ይኖረናል? "እኛ እስካልተስማማን ድረስስ እንዴት አብረን እንጓዛለን?" በ... በዓለም-ዙሪያ፡ በ—በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት፡ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት፡ ሕብረቱ እንዴት ሊሆን ነው? በሚሊዮኖች የሚቈጠሩ ኪሎ ሜትሮች የተላየን ሆነን ሳለ፡ እንዴት አንድ እንሆናለን? አያችሁ? እንዴት እናደርገዋለን? ወንጌላውያኖቻችን፡ **ይህም**፡ **ያም**፡ እና **ያም፡** ሁሉም በአንድ ላይ፡ አሁንም ከእንደዚህ ዓይነት ከተበላሸ ሰብሰብ ጋር አብረዋል።

248 አምላክ ንጹሕ፡ ቅዱስ፡ ያልተበረዘችና፡ ቃሉን ጠብቃ የምትኖር ሚስት ይፈልጋል። መልካም።

249 የኢየሱስ ነቀፌታ ስለ ቃሉ። (በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ እንጨርሳለን።) ኢየሱስ ስለ ቃሉ ተነቅፏል። ወደዚህ ተመልከቱ። መለኰታዊ የሆነው በስጋ የመጣው፡ እንዲህ ያለውን ነቀፌታ፡ እንዴት ሊቋቋም ቻለ? እርሱ በሥጋ የተገለጠ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ነው ነበረ።

250 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ እንዳለው ታውቃላችሁ። "እኛ ዳሰነዋል። መላእክት አይተውታል።" ይህን አስቡት። ጥሞቲዮስ ይመስለኛል እንዲህ ብሎ ያስቀመጠው። አያችሁ? ይህም፡ "እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፡ በሥጋ የተገለጠ፡ ለመላእክት የታየ።"

251 እሱ ሲወለድ መላእክት ነበሩ። መላእክቱ ወደ ታች ወደ ግርግም ሲመለከቱ፡ እግዚአብሔርም በሥጋ ተገልጦ ሲያዩ እንዴት እንደተመለከቱ እና እንደተደሰቱ። አሜን። "ዛሬ፡ በዳዊት ከተማ፡ አዳኝ ክርስቶስ ተወልዷል፡" እያሉ መጮኻቸው ምንም አያስደንቅም። መላእክት ተደሰቱ፡ በይሁዳ ኰረብቶች ላይ፡ ታላላቅ ክንፎቻቸውንም በአንድነት ወዘወዙና፡ እንዲህ ዘመሩ፡ "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፡ ሰላም በምድር፡ ለሰውም በጎ ፈቃድ።" ሲገለጥ ለማየት፡ ይከታተሉት የነበረውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል አይተዋል። እዚያው ነበር።

252 አሁን፡ ታውቃላችሁ፡ ሰይጣን ይህን አላመነም። "አንተ ከሆንክ፡" አለው...

መልአኩም፡ "እርሱ ነው" አለ። ልዩነታቸው ያ ነው።

"አንተ ከሆንክ፡ **እንዲህ-እና-እንዲህ** አድርግ። ይህን ስታደርግ እንይህ።

መልአኩ ግን፡ "በዚያ አለ" ብሏል።

253 ጠቢባኖቹ በሃይማኖታዊ ሳይንሳቸው፡ እንዲህ አሉ፡ "እሱ በዚያ አለ" አሉ። አሜን።

254 አርኪኦሎጂስቶች እና ሁሉም ነገር ዛሬ እነዚህን ነገሮች እየቆፈሩ ያሉት፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት የተተነበዩ፡ የሚፈጸሙ ነገሮች ሰላሉ ነው። እና ይሄው፡ እየቆፈሩ ነው። መቼም ቢሆን...

255 ጴንጤናዊው ጲላጦስ በምድር ላይ እንደነበረ የሚናገር ታሪክ የለም። ይህን ታውቃላችሁ? አንዳንዶቻችሁ የትምህርት ቤት ልጆች ጴንጤናዊው ጲላጦስ በታሪክ ውስጥ የት እንዳለ ንገሩኝ። አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ደግሞ እንዲህ በማለት ይሳለቁበታልና ያፌዙበታል፡ እንዲህ አሉ፡ "የ—የሮማ ቄሣር፡ ወ—

ወይም ጴንጤናዊው ጲላጦስ የሚባል፡ ገዢ ኖሮ አያውቅም” ይላሉ። ነገር ግን ከስድስት ሳምንታት በፊት፡ ገዢው፡ ጴንጤናዊው ጲላጦስ የሚል፡ የማዕዘን ድንጋዩን አወጡ። ኦህ፡ ማይ! ከንቱዎች!

256 እነሱም፡ “በግብፅ ታሪክ ውስጥ፡ ራምሴስ የሚባል የለም” አሉ። ነገር ግን አንድ ድንጋይ አገኙ፡ አርኪኦሎጂ፡ ራምሴስ፡ ሁለተኛው ይላል። ልብ በሉ።

257 እነዚያ ግምቦች ፈጽሞ እንዳልፈርሱ ተናግረዋል። የአርኪኦሎጂ ባለሙያዎች ዙሪያውን እየቆፈሩ ነበር፡ እና፡ የሚታወቀው የመጀመሪያው ነገር፡ ቈፈሩ፡ መለከት በተነፋበት፡ በኢያሪኮ ውስጥ ግድግዳው በወደቀበት ቦታ፡ ታውቃላችሁ። “ይህ አፈ ታሪክ ብቻ ነው፡ ያኔ ድሮ፡ አንድ ሰው የዘመረው ዝማሬ ነው፡” አሉ። አዎን። ፌዘኞቹ እንደዚያ አሉ። “ይህ አፈ ታሪክ ብቻ ነው። የወደቀ ግንብ መኖሩ፡ ኢያሱም መለከቱን መንፋቱ፡ ወደ ግምቡ መሮጣቸው የሚገልጽ በፍጹም የለም። እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ አልነበረም” ይላሉ። እናም አንድ ታላቅ የክርስትና አርኪኦሎጂስት መቆፈሩን ቀጠለ፡ ምክንያቱም ይህ መፈጸሙ ያውቅ ነበር። ሌሎቹ ከነበሩበት ከሰላሳ-ጫማ፡ ወደ ታች ቆፈረ። ቃሉ እንደተናገረው፡ ቅጥሮች እርስ በርስ፡ ተደረማምሰው ነበር።

258 እንዲህ አሉ፡ “ዳዊት ባለ ክር በገና መሳሪያውን፡ መጫወቱን የሚገልጽ ነገር የለም፡ ምክንያቱም የክር ሙዚቃ እስከ አሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ አይታወቅም ነበርና።” እንዲህ አሉ፡ “እንደዚህ ያለ ነገር በፍጹም አልነበረም” አሉ። የክርስትና አርኪኦሎጂስቶች፡ በግብፅ ውስጥ ቆፈሩት። ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት፡ የክር ሙዚቃ መሣሪያዎች ነበሯቸው። አሜን። ኦህ፡ ማይ!

259 የዕብራይስጥ ልጆች ድንጋይ እና የመሳሰሉትን፡ ከገለባ ስለማዘጋጀታቸው፡ እንዲህ አሉ፡ “እንደዚህ ያለ ነገር አልነበረም” አሉ። የአርኪኦሎጂ ባለሙያዎች በዚያ ለመቆፈር ሄዱ። ምን አገኙ? ይህ ሳይንስ ነው። ምን አገኙ? ዕብራውያን የገነቡት የከተማው ግንቦች፡ የመጀመሪያው የድንጋይ ንብርብር ረዥም ገለባዎች ነበሩት፣ ሁለተኛው ደግሞ በትንሽ በትንሽ የተቆራረጡ የእንጨት ቊርጥራጮች ነበሩት፥ ሦስተኛው ደግሞ ምንም ዓይነት፡ ገለባ አልነበረውም። ኦህ፡ ማይ!

> መንግስታት እየፈረሱ፡ እስራኤል ነቅታለች፡
> ነቢያት ያሉት ምልክት ሁሉ ሆነላት፥

260 አዎ፡ ወዳጄ። ሁሉም ነገር ወደ እኛ ደርሷል፡ ወንድሜ፡ እኅቴ። ለምንድን ነው? ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ፡ የፊልም ዓለም አሁን ያደረገውን ከዚህ በፊት አላደረገም። የሴሲል ዴሚል **አስርቱ ትእዛዛት** ታሪክ እስክሪን ላይ መጣ። የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት **በቤን ሁር** በኩል እስክሪን ላይ ታይቷል። **ታላቁ አሳ አጥማጅ**፡ በሚል ርዕስ የጴጥሮስ መቀየር እስክሪን ላይ ታይቷል። እነዚህም ሁሉ ሃይማኖታዊ ድራማዎች፡ ፊልሞች እምቢ ብለው፡ እውነታውን አቆሸሹትና፡ ጣሉት። ነገር ግን፡ እግዚአብሔር፡ በታላቅ ኃይሉ፡ በተመሳሳይ መልኩ፡ አፍረጠረጠው።

261 አሁንም፡ ከዓመታት በፊት ስለ እኔ፡ የተነገሩትን ነገሮችን፡ ድሃው፡ ምስኪኑ፡ ተራው የእግዚአብሄር አገልጋይ፡ “ማድረግ ያለብኝን ነገሮች የነገረኝ፡ ብርሃን

መጣ፡” ስላልኩ። ሰዎች ሳቁና፡ “ጭንቅላቱ ትንሽ ለቋል” አሉኝ። አሁን ፎቶ ግራፉ ወጣ። ሳይንስ አነሣው። ይኸው አለ። እውነት ነው።

“ሴቲቱ በሞት ጥላ ውስጥ ናት፡” አልኩኝ።

262 እነርሱም “ጥላ፡ አሁን፡ ይህ ከንቱ ነገር ነው። በአዕምሮው ውስጥ ፈጥሮት ነው፡” አሉ።

263 ይኸው ፎቶ ግራፉ። እግዚአብሔር ድንጋዮቹ እንዲጮሁ ያደርጋል። የሚሻውን ሁሉ ያደርጋል።

264 ኢየሱስ፡ የቃሉ ነቀፌታ። መለኰታዊ የእግዚአብሔር ልጅ፡ አማኑኤል ቆመ፡ እንዴት ያለ ነቀፌታ ነው! የማያምን ኃጢአተኛው እርሱን አሰሮ፡ ፊቱ ላይ ተፋበት፡ ጢሙንም ነጨ፡ በዚህ ሁሉ ትንፍሽ እንዳይል ያስፈራራዋል። ስለ ቃሉ ምክንያት መነቀፍ! ኡህ-ሁህ። ምን? የአባቱን ቃል ለመፈጸም። ኦህ! ነገር ግን፡ የሞት ነቀፌታ መቋቋም እንደነበረበት፡ አስታውሱ። እግዚአብሔር፡ ኃጢአተኛን ለማዳን መሞት ያለበት ብቸኛ እሱ ሲሆን፡ እሱ ግን የማይሞት ነው። ሌላ ማንም፡ ሁለተኛም ሆነ ሦስተኛ ሰው፡ ይህን ማድረግ አይችልም። ይህን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እሱም ይኸው መጣ።

265 ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “ከሰማይ ከወረደ በቀር ወደ ላይ የወጣ ማንም የለም፡ እርሱም አሁን በሰማይ ያለው የሰው ልጅ ነው።” አሜን።

266 እነሱም “አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ” አሉት።

እርሱም “እነሱ’ማ ሞቱ፡” አላቸው።

“አንተም የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ትላለህን? ”

267 ኢየሱስም “አብርሃም ከመወለዱ በፊት፡ **እኔ ነኝ**። እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ። እኔ **እኔ ነኝ**፡” አላቸው።

268 እነርሱም፡ “አንተ ገና ኀምሳ ዓመት እንኳ ያልሞላህ፡ ‘አብርሃምን አይቻለሁ ትላለህ’ ትላለህን? ”

269 እርሱም፡ “አብርሃም ከመወለዱ በፊት፡ **እኔ ነኝ**” አላቸው። ከዚያም ኃጢአተኞች አሰሩት፡ የሃይማኖት ተቋማት፡ እንዲያስሩት አደረጉ።

270 ታስታውሳላችሁ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ይህች ባለጸጋ የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን፡ እርሱን ከቤተክርስቲያን፡ እንኳ፡ አስወጥታለች። አሁን የት እንዳለ አያችሁ? ስለዚያ ሰርዓት ለምን እንደምጮህ ታያላችሁን?

271 ኢየሱስ ኃጢአተኞች እንዲያስሩት የፈቀደው ለምንድን ነው? ቃሉን ለመፈጸም፡ በመሞት፡ ለእግዚአብሔር የሞት ነቀፌታን ለማምጣት። እግዚአብሔር መሞት ነበረበት። መሞት እንዲችል፡ ሥጋ መሆን ነበረበት። ኢየሱስም ይህን ያውቅ ነበር። ስለዚህ ጉዳይ ነግሯቸዋል። እንዲህ አላቸው፡ “ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፡ እኔም መልሼ አነሣዋለሁ” አለ። ሌላ ሰው ያነሣዋል አይደለም። “አነሣዋለሁ። በሦስት ቀናት ውስጥ፡ እንደገና መልሼ እሰራዋለው። አፍርሱት፡ እኔ አነሣዋለሁ። ዮናስ ለሦስት ቀንና ለሦስት ሌሊት፡ በአሳ ነባሪ ሆድ ውስጥ እንደነበረ ሁሉ፡ የሰው ልጅም እንዲሁ በምድር ልብ ውስጥ መሆን አለበት።” እነሱም መረዳት እንኳ አልተረዱትም። አያችሁ? በቃሉ ምክንያት፡ ተ—ተነቅፎ ነበር።

272 አሁን፡ ዳግመኛ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ለመነሳት፡ እስከ ሞት ድረስ ተሳለቁበት። ለዘላለም ሕይወት ይነሣ ዘንድ፡ በመጀመሪያ መገደል ነበረበት፡ እንዲሁም እርሱን ለሚቀበሉት፡ የሰው ልጆች ሁሉ (በእሱ መልክ የነበሩትን) ወደ ዘላለማዊ ህይወት እንዲወሰዳቸው መገደል ነበረበት። እያችሁ? ሰው ሆነ፡ ቤዛ የሚሆን ዘመድ ሆነ፡ ከእርሱ በፊት ባልንጀሮቹ ባሮቹ እንዳደረጉት ሁሉ፡ የተሳለቁበትን፡ ያፌዙበትን ነቀፋ ሁሉ መቋቋም ነበረበት። እንደ ሙሴ፡ እንደ ኖህ፡ እንደ ሌሎቹም ሁሉ ያንን ነቀፋ እንደተቋቋሙት፡ እርሱም ያንን ነቀፋ መቋቋም ነበረበት። ለምን? ቃል በእርሱ ዘንድ ስለነበረ፡ እርሱ ቃል ነበር። ለዚህም ነው ከመቼውም ጊዜ በላይ ያሾፉበት። እርሱ መለኮትና ቃሉ ራሱ ነበር። ሃሌ ሉያ! እርሱን ያደረገው ያ ነው።

273 ኢየሱስም፡ "እናንተ ግብዞች" አላችው። እንዲህ አለ፡ "እናንተ የነቢያትን መቃብር ትሠራላችሁ፡ እዚያ ውስጥ ያወረዳችኋቸው እናንተ ራሳችሁ ናችሁ። እነሱ የእግዚአብሔር ቃል ይዘው መጡ፡ እናንተም አላመናችሁም። በእያንዳንዳቸው ጥፋተኞች ናችሁ።"

274 በፊኒክስ፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ሌላ ቀን አንድ ቃል እሰብካለሁ፡ ይህ ትውልድ ኢየሱስ ክርስቶስን በመግደሉ፡ ዳግም በመስቀሉ ምክንያት እከሰዋለሁ፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ በአገልጋዮች ማኅበር ፊት ክስ አቀርባለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ጥፋተኞች ናቸው፡ ምክንያቱም ኢየሱስን ዳግመኛ ሰቅለውታል። አዎ፡ ወዳጄ። ሁሉንም እከሳቸዋለሁ።

275 ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን፡ ከሰሳቸው። እንዲህም አለ፡ "በኃጢአተኞች እጅ የሕይወትን አለቃ ሰቀላችሁት፡ እግዚአብሔር ግን አስነሣው። እኛም ምስክሮች ነን።" ክስ አቀረበ።

276 በእግዚአብሔርን ቃል፡ እያንዳንዱን የሃይማኖት ተቋም እከሳቸዋለሁ፡ በምድርም ላይ ያለውን እያንዳንዱን ሰው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ጥፋተኛ እንደሆኑ እከሳቸዋለሁ። በዚያ ቀን ጠበቃ እንድሆን እግዚአብሔር ይርዳኝ። አሜን። አዎን።

277 ኦህ፡ ፌዘኞች አሾፉበት። ነቀፉት። እርሱ ከቃሉ ጋር ጸና። አሜን። ኦ! ያደረገውን ተመልከቱ። የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፡ ነገር ግን የኃጢአትን ሞት ለማስወገድ ሞትን ተቀበለ። ያንን ማድረግ ነበረበት። ሊ... ሊሞት የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው። ይህንንም አደረገ፡ ተቋቋመም፡ ምክንያቱም የቀሩት ሁሉ ያንን ስላደረጉ።

278 ምክንያቱም፡ በዚያ የነበሩት ሁሉ አነስተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነበራቸው። ምክንያቱም፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏልና። "የ—የእግዚአብሔር ቃል ወደ ነቢያት መጣ። ከመካከላቸው የትኛው ነው፡" እንዲህም አለ፡ "አባቶቻችሁ፡ የተደራጁ ሃይማኖታችሁ፡ በድንጋይ ወግረው አልገደሉምን? ከመካከላቸው ነቢያትን የተቀበለው የትኛው ነው? ከዚያ እነሱ ከሄዱ በኋላ መቃብራቸውን ትሰራላችሁ።" እንዲህ አለ፡ "እነሱን እዚያ ውስጥ በማውረዳችሁ ጥፋተኞች ናችሁ።"

279 ከዚያም የወይን እርሻን ምሳሌ ተናገረ፡ አገልጋዮችም መጡ። አስቃዩዋቸው፡ በመጨረሻም እንዲህ አሉ፡ "አሁን ልጁን እንገድለዋለን፡ ወራሹ ነውና።" እያችሁ? ኦህ፡ ያን ሲያዩ ተቆጡ። እያችሁ?

280 ነቀፋውን ግን መቋቋም ነበረበት። እዚህ እርሱ ራሱ ታሰረ፡ የዘላለም ሕይወትን መልሶ ለማምጣት፡ ለመሞት፡ ወደ ሞት አመራ። ክብር ለእግዚአብሔር! ኦህ፡ እንዴት እንደምወደው! ዘላለማዊ ሕይወትን መልሶ ያመጣል፡ እንዲሁም በዘመናት ሁሉ፡ ከቃሉ ጐን የቆመውንና ነቀፋን የተቀበለውን እያንዳንዱን የእግዚአብሔር ልጅ ያስነሣል። በትክክል።

281 እሱ ባይመጣ ኖሮ፡ ኖህ አይነሳም ነበር። እሱ ባይመጣ ኖሮ፡ ኤልያስ ተመልሶ አይመጣም ነበር። እሱ ባይመጣ ኖሮ፡ ባይችል ኖሮ… ባይመጣ ኖሮ፡ ኖህ በጭራሽ አይነሳም ነበር። ምክንያቱም፡ እርሱ ራሱ ነቀፌታውን በራሱ ላይ ለመሸከምና፡ ለእያንዳንዱ ለተነገረው ለእግዚአብሔር ቃልና፡ እነዚህ ጻድቃን ሰዎች ለቆሙት ነገር ሞትን ለመሞት፡ አስቀድሞ የተወሰነ በግ ነበር። እንደዛ መሆን ነበረበት። ሌላ ማንም ሊያደርገው አይችልም። ለዚያ ቃል የቆመውንና፡ ነቀፌታውን የተሸከመውን፡ የእግዚአብሔርን ልጅ ሁሉ ሊቤዥና ለዘላለም ሕይወት ሊሰጥ እግዚአብሔር ራሱ መጥቶ ቦታውን ወሰደ። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ፡ በዘመኑ ሁሉ፡ ነቀፌታውን ቢቋቋም፡ ማንም ሊቤዠው አልቻለም፡ ነገር ግን በእምነት አዳኙ ሲመጣ አየ።

282 ኢዮብም አየው። ኢዮብም በዚያ ቆሞ፡ እንዲህ አሉት፡ "ኦህ፡ አንተ በሰውር ኃጢአተኛ ነህ። እግዚአብሔር እየቀጣህ ነው፡ ምክንያቱም ሰውር ኃጢአተኛ ነህ" አሉት።

283 እንዲህም አለ፡ "አዳኜ ህያው እንደሆነ አውቃለሁ። በመጨረሻው ዘመን በምድር ላይ ይቆማል። ምንም እንኳን የቆዳ ትሎች ይህንን አካል ቢያጠፉም፡ ነገር ግን በሰጋዬ፡ እግዚአብሔርን እያለሁ።"

284 ሚስቱም፡ "ለምን እግዚአብሔርን ተሳድበህ አትሞትም? " አለችው፡ "አሳዛኝ ምስኪን ሰው ትመስላለህ፡" አለችው።

285 እርሱም፡ "እንደ ሰነፍ ሴት ትናገሪያለሽ" አላት። አሜን። እንደዛ ነበር። "ሕያው እንደሆነና፡ በመጨረሻው ዘመንም እንደሚነሣ አውቃለሁ።"

286 ኢየሱስ ባይመጣ ኖሮ፡ ኢዮብ መቤዡት አይችልም ነበር፡ ምክንያቱም እርሱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የታረደው በግ ነበር። ሰፍራውን አወቀ። አቋሙን አወቀ።

287 ማርያም በዚያ ቀን ስትወጣ፡ ያንን ቦታ ያወቀችው፡ በዚህ ምክንያት ነው። እ… እርሷም፡ "እ… አንተ እዚህ ብትኖር ኖሮ፡ ወንድሜ አይሞትም ነበር" አለች።

እርሱም፡ "ወንድምሽ ይነሣል" አላት።

እርሷም፡ "አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ በትንሣኤ ቀን ይነሳል። ጥሩ ልጅ ነበር" አለች።

ኢየሱስም፡ "ትንሣኤ ግን **እኔ ነኝ**። ይህን ታምኛያለሽ? "

288 እርሷም፡ "አዎ፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ ወደ አለም የመጣህ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ አምናለሁ" አለች።

እርሱም፡ "የት ነው የቀበራችኹት? " ኦህ! ይሄው። ኧሃ-ሃም።

289 ያን ጊዜ ተረዳች። ያቺ ምስኪን ሴት እንዲህ ስትል አልነበረም። ከእርሷ ውስጥ ሰባት ሰይጣኖች ወጥተዋል። ትዕቢትንና ጭንቀትን ሁሉንም ነገር፡ ከእርሷ ሊያርቅ የሚችለውን፡ የእግዚአብሔርን ኃይል አወቀች፡ ይህም ያንን ትንሽ፡ ራስ ወዳድ የሁለተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት መንፈስን፡ ከእርሷ አስወጥቶ

አዲስ ፍጥረት የሚያደርጋት የእግዚአብሔር ሃይል ነው። ሰባት አጋንንት አወጣላት። እነሱም ሴቶች እርሱን የተቀበሉት፡ ማን እንደሆነ አወቁ።

290 ምን ሊያደርግላቸው እንደሚችል ያውቃሉ። ዛሬም፡ እንዲሁ። ብቻ ተቀበሉት። ያ የሚቀጥለው ነገር ነው።

291 እሱ አለ። እንዲህ አለች። ሞ... ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ። ኦህ!

292 ለተመሳሳይ ቃል መከራን የሚቀበል ሁሉ፡ የሞተው ለዛ ነው። ይህን ለማድረግ፡ ሊሞት የሚችለው እርሱ ብቻ ነበር፡ እርሱ ቃል ነበርና። እርሱ ቃል ነበር፡ ቃሉም ተገለጠ። ሌሎቹ ሁሉ ትንሽ ጠብታ ነበራቸው፡ ነገር ግን እዚህ የእግዚአብሔር ሙላት፡ በእርሱ ነበር። ዛሬም ያው ነው። ዕብራውያን 13:8፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።" አዳምጡ።

293 በእውነቱ፡ እየዘጋሁ ነው። ልዘጋው ነው፡ በቃ መጨረስ አለብኝ። ሰአቴን አልፌያለሁ።

294 አንድም ቃል ጽፎ አያውቅም። ጽፏል´ዴ? [ጉባኤው፡ "አልጻፈም" አለ።—አርታዒ።] አንድም ቃል ጽፎ አያውቅም። ለምን? እርሱ ቃል ነበር። እሱ ምን ነበር? የተጻፉት ቃላት፡ የነዚያ ቃል መገለጫ ነበር። ክብር! ዋው! አሁን ጥሩ ስሜት ይሰማኛል። እርሱ ቃል ነበር። ምንም ነገር መጻፍ አልነበረበትም። እርሱ ቃል ነበር፡ ይህ የተጻፈ ቃል ተገለጠ። ክብር ለእግዚአብሔር! እሱ ዛሬ፡ ትናንት፡ ዛሬ እና ለዘላለም ያው ነው። የተገለጠው፡ ቃል እርሱ ነው።

እንዲህ ትላላችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ይህ ትክክል ነውን? "

295 ያህዌ በዚያ ቆሞ እንደዚያ ባሉ ሞገዶች ላይ ነፋስ ሲነፍስና፡ ለእስራኤላውያን የሚሻገሩበት መንገድ ሲፈጥር ተመልከቱ።

296 በሥጋ የተገለጠውን ያህዌ፡ እንዲህ ሲል፡ "ዝም በል፡ ጸጥ በል" ሲል አዩት። ማዕበሉ ውኆችን ሲመታ፡ ዐውሎ ነፋሱ ሲመጣ፡ እንደዛው፡ ዲያብሎስ ሁሉንም ነገር ሲልክባቸው፡ እርሱም፡ "ዝም በል፡ ጸጥ በል" አለው። እርሱም ታዘዘለት፥ ነፋሱና ሁሉም ታዘዙለት። እርሱ ያህዌ ነበር። አሜን።

297 በዚያ ከአድማስ ባሻገር ቆሞ ትንሽ ጠል የሚረጭ ያህዌ፡ ህዝቡ ይመገብ ዘንድ፡ ወደ ምድር መጣ እንጀራም ሆነ።

298 እዚያ ቆሞ አምስት ዓሣ፡ ወይም፡ አምስት ብስኩትና ሁለት ዓሣ ወሰደ፡ አምስት ሺህም መገበ።

299 እርሱ ቃል ነበር። አሜን። አሜን። እርሱ ቃሉ ነው፡ ሁልጊዜም ቃል ይሆናል። እኔና ቤቴ፡ ቃሉን እናገለግላለን።

ኦህ፡ እሱን ማየት፡ ፊቱን ማየት እፈልጋለሁ፡  
በዚያም የማዳን ጸጋውን ለዘላለም ዘምሩ፣  
በክብር ጎዳናዎች ላይ፡ ድምፄን ከፍ ላድርግ፥  
ጭንቀት ሁሉ አልፎ፡ በመጨረሻ ቤት፡ ሁል ጊዜ ደስታ  
ይሆናል።

300 ኦህ፡ ማይ! አዎን። ስለ ቃሉ ነቀፌታን ተሸከሙ። ከቃሉ ጋር የሚሄድ ይነቀፋልና። ከቃሉ ጋር በትክክል ቆዩ፡ ነቀፌታውን ተሸከሙ።

እንጸልይ።

301 ኢየሱስ ሆይ፡ በቀደም ሌሊት፡ ጌታ ሆይ፡ እንደተማጸንኩ፡ “ኦህ ኢየሱስ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? ጌታ ሆይ፡ ምን ላድርግ? እነዚህን ነገሮች እያየሁ፡ የምንኖርበትን ጊዜ እያወቅሁ፡ ጌታ ሆይ፡ ምን ላድርግ? ምን ማድረግ እችላለሁ?”

302 ስለ ታናሺቱ ቤተ ክርስቲያኔ እጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ በራዕይ ውስጥ ስላየኋቸው ትናንሽ ወፎች አስባለሁ፡ የነበሩትን ነገሮች ሁሉ፣ ሌሎችም ወፎች፡ ታላቅ ነገሮች ነበሩ። ነገር ግን ከነሱ ውስጥ ሶስት ደረጃዎች ነበሩ፡ ጌታ ሆይ። ነገር ግን መላእክት በገቡ ጊዜ፡ ምንም ወፎች አልነበሩም። ትንንሾቹ መልእክተኞች ድንቅ ነበሩ፡ ጌታ ሆይ፡ ነገር ግን አንድ ነገር ሊሆን እንደሆነ አምናለሁ። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። ቅረጸንና መንገድህን እንድንከተል አድርገን። እ—እኛ ሸክላዎች ነን። አንተ ሸክላ ሠሪ ነህ።

303 በዚህ በገና ዋዜማ፡ ጌታ ሆይ፡ ስለ እግዚአብሔር ስጦታ፡ እግዚአብሔር ስለሰጠን አመስጋኞች ነን። በልባችን እንደምናምነው፡ አንዳንድ አርማዊያን፡ የራሳቸውን የባህል፡ ቀናቸውን በ—በመቅረጽ ልክ እንደ ገና እንዲመስል ለማድረግ ሞክረዋል፡ እኛ ግን የገና አባትና የገና ዛፎችንና ጌጣጌጦችን በማድረግ በዚያ መንገድ አ—አንመጣም። እኛ ግን እኛን ለመበዤት፡ እንደ እኛ ሥጋ ለብሶ፡ በመካከላችን ያደረውን፡ የሰማይን አምላክ ለማምለክ፡ በጌታ በእየሱስ ሰም፡ እንመጣለን፥ ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ሊያመጣን ዘንድ፡ አማኑኤልን የአለማዊ ተቋም እንዲገድለው በማድረግ፡ የሰሙን ነቀፋ፡ የመስቀሉን ነቀፌታ ተቀበለ።

304 ጌታ ሆይ፡ እኛ ማን ነን? ከነቀፌታ ሁሉ ለመራቅ፡ እኛ ማን ነን? አምላክ ሆይ፡ ደፋር ወታደሮች አድርገን። አባቴ ሆይ፡ እነዚህን ቃላት ለአንተ አደራ እሰጣለሁ። እነሱ ተሰብረው ልክ እንደእኔ፥ ደክሟቸው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፡ አባት ሆይ፡ ተቀምጠው የሰሙት እነዚህን ሰዎች ሸልማቸው። ጌታችንንም ያስነሳው፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ እርሱም ለእኛ አጋኝ ያደረገው ያ ሃይል፡ ጌታ ሆይ፡ በዚህ ያለውን መንፈስ ሁሉ፡ ወደ ጌታ ኢየሱስ መምጣት ለማቅረብ ህይወትን ይስጥ። ይሁን፡ አባት ሆይ።

305 በመካከላችን ያሉትን የታመሙትን እና የተጎዱትን ፈውሳቸው። ልባቸው-የተሰበረባቸው ጠግን። ጌታ ሆይ፡ በ… በጣም በብዙ ነገር ውስጥ አልፈናል፡ በከባድ ጦርነቶች የተነሳ፡ በልቤ ላይ ብዙ ጠባሳዎች አሉ፡ ጌታ ሆይ። የሸመገልኩ አርበኛ ነኝ። እርዳኝ፡ ጌታ ሆይ። እርዳታህን እፈልጋለሁ። ምናልባት ይህ ሁሉ ስልጠና ለአንድ ዓላማ ሊሆን ይችላል። እንደ ሆነም አምናለሁ፡ ጌታ ሆይ። አምላኬ ሆይ፡ እርዳኝ። ይችንም ቤተ ክርስቲያን እርዳት። ሁላችንንም፡ ባርከን።

306 ትንንሽ ልጆችን ባርካቸው። ዛሬ ብዙዎቹን እያሰብኩ ነው፡ ትናንሾችን፡ ምስኪን ትናንሾችን እዚያ ምንም ስጦታ እንደማየገኙ እያሰብኩ ነው። ከ—ከእነሱ ጋር እንድትሆን እንድትረዳቸውም እጸልያለሁ። የዘላለም ሕይወት፡ ስጣቸው ጌታ ሆይ። ያ ታላቅ ነገር ነው… የምንፈልገው የገና ስጦታ ያ ነው፡ ይህም በልቤ ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ እንዲነግስ እና እንዲመራ ነው። እኔ የምፈልገው ይህንን ነው፡ ጌታ ሆይ።

307 አሁን ሁላችንንም፡ ባርከን። እነዚህን ቃላት ለአንተ አሳልፈን እንሰጣለን። በፈለጉት ቦታ ይረፉ፡ ጌታ ሆይ። ልቦች በከፈቱበት ቦታ ሁሉ፡ በኢየሱስ ስም፡ ታላቅ የመዳን ጊዜ ያምጡ። አሜን።

308 ስ... ስንቶቻችሁ ትወዱታላችሁ? እንዲህ የምትጣደፉት፡ በርግጥ? ኦህ፡ እወደዋለሁ! እወደዋለሁ። “ጌታ ሆይ፡ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? ”

309 ዛሬ ማታ ያለውን አገልግሎት አትርሱ። አሁን ክሪስማስ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? ኦህ፡ **ይህ** የኔ ክሪስማስ ስጦታ ነው። **ይህ** ያ ቃል ነው። ጌታ ሆይ፡ ራሴን ካወጣሁ፡ ቃልህ እንዲገልጠው፡ ራሱ እዚህ ወጥቶ እንዲገልጠው፡ ራሴን ከመንገድህ፡ ማውጣት **ከቻልኩኝ**፡ የ—የማውቀው ትልቁ ነገር ያ ነው።

310 አሁን ለልጆቹ መስጠት የፈለጉትን ነገሮችን ያዘጋጁ ይመስለኛል። አሁን አገልግሎቱን ወደ ወንድም ኔቪል እመልሳለሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

ወንድም ኔቪል።

62-1223 ስለ እግዚአብሔር ቃል መነቀፍ
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱሰ ክርሰቶሰን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይሰ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግሰ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማሰቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማሰቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org